ምዕራፍ

# 12

# የሐዋርያነት ስጦታ

*"...እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት... እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ።" (ኤፌ. 4፥11)*

ሐዋርያነት ከአምስቱ "የአገልግሎት ስጦታዎች" መካከል አንዱ ነው። *"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ ነቢያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ"* ይላል (ኤፌ. 4፥11)። እነዚህ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች *"የትጥቅ"* ስጦታዎች ይባላሉ። *"የትጥቅ ስጦታ"* የተባሉበት ምክንያት፥ የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) በምድር የክርስቶስ አምባሳደር እንድትሆን፥ ቅዱሳን (አማኞች) አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ የሚያስችል ስጦታ በመሆኑ ነው። ይሄም ስጦታ ራሳችንን የምንጠቅምበት "ሹመት" ሳይሆን፥ ሌሎችን የምናገለግልበት ስጦታ ነው። *"ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን*



*ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ"* (1 ጴጥ. 4፥10)። ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ከመረጠ በኋላ፥ "የእውነትን" ቃል አደራ ሰጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካስታጠቃቸው በኋላ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ ላካቸው። በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ የዓለም ጨውና ብርሃን እንዲሆኑ፥ በጠባያቸውና በግብረ ገብ ሕይወታቸው ፍጹም የተለዩ ሆነው ለዓለም ደህንነት የሚሆነውን ወንጌል እንዲሰብኩ አዘዛቸው። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በወንጌሎች ውስጥ፥ "ደቀ መዛሙርት" ተብለው ሲጠሩ እናያለን። "በደቀ መዝሙርና" እንዲሁም "በሐዋርያነት" መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ልዩነት እንዳለ ያምናሉ። "ታላቁ ተልኮ" አማኞች ሁሉ "ደቀ መዝሙር" እንዲሆኑ ያዛል። ሁሉም ሐዋርያ ይሆናሉ ግን አይደልም። "ሐዋርያ" የሚለው ቃል ስጦታቱ ሳይገለጽ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አራት ጊዜ ተጠቅሶ እናያለን (የሐዋ. 1፥26፤ ሮሜ 1፥5፤ 1 ቆሮ. 9፥2፤ ገላት. 2፥8)።

## 1. ሐዋርያነት ምንድነው?

"ሐዋርያነት" ሥልጣን (office) ነው? ወይንስ ስጦታ (gift)? ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 12፥28ና እንዲሁም በኤፌሶን 4፥11 ላይ "ሐዋርያነት" የአገልግሎት ሥልጣን እንዲሁም ስጦታ እንደ ሆነ ይገልጻል። ሁለቱም አብረው የሚሄዱ እንጂ የተለያዩ አይደሉም። "ሐዋርያነት" የአገልግሎት ሥልጣን ብቻ ሳይሆን፥ ስጦታም እንደ ሆነ የሥነ መለኮት አዋቂዎች ይናገራሉ። በአዲስ ኪዳን *"ሐዋርያ"* የሚለውን ሀሳብ የምንረዳው፥ የተለየ አገልግሎት እንዲፈጽም ከጌታ ጥሪ ተደርጎለት ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄድ የተላከውን ሰው ነው። "መልዕክተኛ" የሚለው ቃል "ሐዋርያ" የሚለውን ሀሳብ በከፊል ቢገልጸውም፥

"የሐዋርያነት ስጦታ" ያለውን የስልጣን አቋም አያሳይም። ጳውሎስ *"...በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል..."* (ኤፌ. 2፥20) ሲል ምን ማለቱ ነው? እምነታችን የተመሠረተው ሐዋርያት በተናገሩትና ባስተማሩት ትምህርት ላይ እንደ ሆነ ሲገልጽ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ብንፈልግ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፏቸውን መልዕክቶች ማንበብና ማጥናት እንደሚያስፈልገን እናውቃለን። በዚህ ዓይነት "ሐዋርያት" ሲል፥ የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያትን እንደ ሆነ እናያለን።

## 2. ከአሥራ ሁለቱ ሌላ ሐዋርያት ነበሩ?

ከአሥራ ሁለቱ ሌላ "ሐዋርያት" ተብለው የሚጠሩ ሌሎች እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጳውሎስ ሐዋርያ ነበር። በርናባስ ሐዋርያ ነበር (የሐዋ. 14፥14)። ያዕቆብ ሐዋርያ ነበር (ገላት. 1፥19)። ሲላስና ጢሞቴዎስ ሐዋርያት ነበሩ (1 ተሰሎ. 1፥1፣ 2፥6)። አንዲራኒቆንና ዩልያን ስመ ጥሩ ሐዋርያት ነበሩ (ሮሜ 16፥7)። ሌሎች ሀሰተኛ ነብያትም እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (2 ቆሮ. 11፥13)። ከአሥራ ሁለቱ ሌላ ሐዋርያት ተብለው የሚጠሩ ሌሎች መኖራቸውን ስናይ፥ "የሐዋርያነት ስጦታ" በመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ላይ ብቻ እንዳላበቃ እንገነዘባለን። የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ግን ልዩ እንደነበሩ እናውቃለን።

## 3. የመጀመሪያዎቹ፥ "ሐዋርያት" ተብለው ለመጠራት ያበቃቸው (qualification) ምንድነው?

### 3.1. ከመጀመሪያው ጀምሮ ከክርስቶስ ጋር የነበሩ በመሆናቸው

በይሁዳ አስቆሮቱ ምትክ ሌላ ሰው ለመምረጥ ደቀ መዛሙርቱ በተሰበሰቡበት ወቅት፥ ጴጥሮስ የሚመረጠው ሰው ምን ዓይነት እንደ ሆነ ሲገልጽ *"...ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች..."* አለ (የሐዋ. 1፥22)።



### 3.2. የክርስቶስን ትንሳኤ መመስከር ስለቻሉ፥ (1ኛ ቆሮንቶስ 9፥1፣ 15፥8)

ጴጥሮስ፥ በይሁዳ ምትክ የሚመረጠው ሰው ምን ዓይነት ሰው መሆን እንዳለበት ሲዘረዝር፥ *"...ከእኛ ጋር የትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል"* ይላል (የሐዋ. 1፥22)።

### 3.3. ምልክትና ድንቅ ነገር፥ ማድረግ ስለቻሉ፥ (2ኛ ቆሮንቶስ 12፥12)

በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ከወረደባቸው በኋላ በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅ ነገሮች ይፈጸሙ ነበር። *"ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ"* (የሐዋ. 2፥43)። ሦስት ምዕራፍ ዝቅ ይልና *"በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር"* ይላል (የሐዋ. 5፥12)። አሁንም ሦስት ምዕራፍ ዝቅ ብሎ *" ...ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ..."* ይላል (የሐዋ. 8፥18)። እነዚህ ድንቅ ነገሮች በሐዋርያት እጅ የተፈጸሙት፥ ሐዋርያነታቸው እውነተኛና አስተማማኝ መሆኑን ለመግለጽ ነበር። *"...በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር፥ በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ"* ይላል (2 ቆሮ. 12፥12)። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሐዋርያት ሲሞቱ፥ ምልክቶቹም ወዲያው ጠፉ ብለው ያምናሉ።

### 3.4. ሐዋርያ እንዲሆኑ በመጠራታቸው፥ (ሮሜ 1፥1)

ጳውሎስ *“ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ”* ሲል፥ “ሐዋርያነት” መጠራትን እንደሚጠይቅ እንገነዘባለን። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ለአገልግሎት መርጦ እንደጠራቸው እናውቃለን። *“ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፤ ወደ እርሱም ሄዱ”* (ማር. 3፥13)። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ *“አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካች ኋለሁ”* (ዮሐ. 20፥21) ብሎ ወደ አገልግሎት እንዳሰማ ራቸው እናውቃለን።

3.5. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመላካቸው፥ (የሐዋ. 13፡3-4)

3.6. ወንጌል ባልተሰበከበት ሥፍራ አገልግሎት የጀመሩ በመሆናቸው፥ (ሮሜ 15፥20)

3.7. ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሲሉ፥ የሌሎችን ባሕልና አኗኗር ተቀብለው መኖር የሚችሉ ስለሆኑ (1 ቆሮ. 9፥19-22) መሆናቸውን እናውቃለን።

3.8. በአማኞች ዘንድ ስጦታ እንዳላቸው በሚሰጡት አገል ግሎት የተመሰከረላቸው በመሆናቸው፥ (1ኛ ጢሞቴ ዎስ 4፥14)።

## 4. በዘመናችን “የሐዋርያነት” ስጦታ አለ ወይ?

ሐዋርያው ጳውሎስ *“እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ... አድርጓል”* (1 ቆሮ. 12፥28) ቢልም፥ በዘመናችን “የሐዋርያነት” አገልግሎት አለ ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ



የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የተለያየ መልስ አላቸው። የሐዋ ርያት አገልግሎት በመጀመሪያዎቹ በአሥራ ሁለቱ ላይ ያበቃ ስለሆነ በዘመናችን የሐዋርያነት ስጦታ ለማንም አይሰጥም የሚሉ አሉ። የሐዋርያነት አገልግሎት በዘመናችንም ይሠራል የሚሉት ክፍሎች፥ “ስጦታው ዛሬም አለ” የሚሉበት ምክንያት አላቸው። የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት በክርስትና ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራ ይዘው የሚቆዩ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ በአዲሲቷ ኢየሩሳ ሌምም የከበረ ሥፍራ እንደሚይዙ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *“ለከተማይቱ ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት፤ በእነ ርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር”* (ራዕይ 21፥14)። ከመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ ሐዋ ርያት ቀጥሎ ሌሎች ሐዋርያት እንደነበሩ ቀደም ሲል ተመል ክተናል (የሐዋ. 1፥26፣ ሮሜ 1፡1፣ 16፥7፣ 1 ተሰሎ. 2፥6)።

በዘመናችን “ሐዋርያት” የሚባሉት ምን ዓይነት መንፈ ሳዊ መሪዎች እንደሆኑ *ፒተር ዋግነር* ሲገልጹ፥ “ለቤተ ክርስቲ ያን መሪዎችና መጋቢዎች ምክር ሲፈልጉ ምክር፥ ጠቃሚ ሀሳብና ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ በማስተዋልና በጥበብ እግዚ አብሔር የሞላቸውና ልዩ ጥሪ ያላቸው ናቸው። በመሪዎች መካ ከል አለመግባባት ሲፈጠር በማስታረቅ ወይንም ስምምነት እን ዲፈጠር የሚረዱ፥ ችግር ሲኖር ችግሩን የመፍታት ችሎታ ያላቸው፥ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን ያገኙና የተከበሩ ናቸው።” በዘመናችን የሐዋርያትን ሥራ የሚ ሠሩት “ሐዋርያት” ተብለው አይጠሩ እንጂ፥ በተለያየ መጠሪያ ስም እንደሚጠሩ እናውቃለን። የተለያዩ “ቤተ እምነቶች” *(denomination)* የተለያየ ስም ሰጥተዋቸዋል፤ ለምሳሌ... ጳጳስ፥ የአውራጃ ወይንም የበላይ ተቆጣጣሪዎች፥ *(District Superintendents)* ፕሬዚደንት፥ ዋና ጸሐፊ፥ ወዘተ. ብለው ይጠሩአቸ ዋል። ይህን ዓይነቱን ስም የሚሰጧቸው *“የሐዋርያነት ስጦታ”*

እንዳላቸው ያመኑባቸውን መሆን ነበረበት። ይሁን እንጂ፣ ብዙ
ዎቹ ይህን ዓይነቱ ሥልጣን የሚሰጣቸው ስጦታቸው ታይቶ
ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያየ ኃላፊነት ውስጥ ለረ
ጅም ጊዜ በመቆየታቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው
የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ ውስጥ የበላይነት በማግኘታቸው ብቻ
ሊሆን ይችላል።

ፒተር ዋግነር በዘመናችን የሐዋርያነት ሥልጣን የያዙ
ትን በሁለት ይከፍሏቸዋል፤

## 1ኛ) በሹመት ሥልጣኑን ያገኙ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ባሉበት የሃይማኖት
ክፍል ውስጥ የያዙት ከፍተኛ ሥፍራ በተለያየ መንገድና ዘዴ
የተገኘ እንጂ፣ ባላቸው ተሰጥኦና ጥሪ መሠረት የተቀበሉት ሥል
ጣን አይደለም። ብዙዎች የሚታዘዙአቸውና የሚያከብሯቸው፣
ሥልጣኑን ስለያዙ እንጂ፣ የመሪነት ስጦታ ወይንም ጥሪ አላ
ቸው ብለው በማመን አይደለም። ሥልጣኑን የሚመለከቱት
እንደ ጥሪና አገልግሎት ሳይሆን፣ እንደ ሹመት ነው። ስለዚህ
በአካባቢያቸው ያሉት ትዕዛዛቸውን የሚቀበሉት በማጉረምረም
እንጂ በደስታና በአክብሮት አይደለም። የቤተ ክርስቲያን መሪ
ነትን በሹመት መልክ የተቀበሉት ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ሁኔታን
አጨልመው የሚያዩ ናቸው። ችሎታ ያላቸው፣ ወይንም በች
ሎታቸው ከእነርሱ የሚበልጡ አንዳንድ ሰዎች በአካባቢያቸው
ካዩ ሥልጣናቸውን የሚወስዱባቸው ስለሚመስላቸው ወይንም
በእነርሱ ዓይን ሲታዩ አነስተኛ የሆኑ ስለሚመስላቸው፣ ያለ
ምክንያት ሲሰጉና ሌላውን ሲጋፉ ይታያሉ።

## 2ኛ) የመሪነት ስጦታ ኖሮአቸው የሚያገለግሉ

ሌሎች ደግሞ በሰዎች ያልተሾሙ፣ እግዚአብሔር ጠር
ቷቸው፣ ስጦታውን ሰጥቷቸው በመሪነት የሚያገለግሉ ናቸው።



በአካባቢያቸው ያሉትና አብረዋቸው የሚያገለግሉት ሰዎች የሚ
ታዘዟቸውና የሚያከብሯቸው፣ ጥሪና ተሰጥኦ እንዳላቸው አይ
ተው እንጂ፣ ሥልጣኑን ስለያዙ ብቻ አይደለም። ሁኔታን አጨ
ልመው የማያዩ፣ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በዙሪያቸው ሲሆኑ
"ሥልጣኔን ይወስዱብኛል" በማለት የሚሰጉ አይደሉም። ስለዚህ
አብረዋቸው ከሚያገለግሉት ጋር ጥሩ ሕብረት ወይንም ግንኙነት
ያላቸው ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ "የሐዋርያነት ሥጦታ"
እግዚአብሔር እንደሰጣቸው ማመን አያዳግትም።

"ሐዋርያት" የምንላቸው የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ
ንና በእነርሱ አካባቢና ዘመን የነበሩትን ብቻ ከሆነ፣ የሐዋርያ
ነት ሥጦታ ወይንም አገልግሎት በእነርሱ ዘመን አክትሟል
ማለታችን ነው። ይህን ዓይነት እምነት ካለን፣ ስጦታው በእኛ
ዘመን አይሠራም ማለታችን ይሆናል። ቀደም ሲል እንደጠቀስ
ነው፣ "ሐዋርያት" እንዲሆኑ ያስቻላቸውን ወይንም ያበቃቸውን
ምክንያት ስንመለከት፣ ይኸውም፣ የክርስቶስን ትንሳኤ ያዩ፣
ልዩ የሆነ መለኮታዊ ራዕይ ወይንም መገለጥ ያገኙ፣ ተአምር
የመሥራት ስጦታ ያላቸው ባይሆኑም፣ "የሐዋርያነት" ስጦታ
ያላቸው ሰዎች በዘመናችንም አሉ። ሐዋርያ የሚለው ቃል
"አፖስቶሎ" ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም
"የተላከ" ማለት ነው። ሐዋርያ ለወንጌል ሥርጭት የተጠራ፣
ግዴታ እንዳለበት የሚሰማው ሰው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ
"ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ!" ያለው ለዚህ ነው። "ሐዋርያት"
ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንዲያሰሙ የተጠሩ ናቸው። "ሐዋርያ
ነት" ምን እንደሆነ የበለጠ ለመረዳት፣ የቀድሞ ሐዋርያት ምን
ዓይነት አገልግሎት እንደነበራቸው መመርመር ነው።

"ሐዋርያት" ብዙ ጊዜያቸውን ከክርስቲያኖች ጋር ያሳ
ልፉ እንደነበረ እናውቃለን። *"...በሐዋርያትም ትምህርትና
በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ፣ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር"*

(የሐዋ. 2፥42) ይላል። ላልዳኑትም ወንጌልን በመስበክ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር (የሐዋ. 4፥8)። ሐዋርያው ጳውሎስ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናትን ከመመሥረቱ ሌላ፥ የመሠረታቸውን እንደ ገና ተመልሶ በመሄድ ያበረታታቸው እንደነበረ እናውቃለን (የሐዋ. 14፥21-23)። እርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲያገለግሉ አንዳንድ አገልጋዮችንም ይልክ እንደነበረ እናውቃለን። ቤተ ክርስቲያንን እንዲያደራጁ፥ (ቲቶ 1፥5)፥ እንዲሁም በትምህርት እንዲያጸኑ (ቲቶ 2፥1፣ 3፥1) ቲቶንና ጢሞቴዎስን አስተማሪና እረኛ በመሆን እርሱ በመሠረተው መሠረት ላይ እንዲሠሩ ይልካቸው እንደነበረ እናውቃለን (ፊልጵ. 2፥19-21)። ጳውሎስ ሌላው በመሠረተው መሠረት ላይ ቀጥሎ መሥራትን ባይቃወምም፥ የእርሱ አገልግሎት ግን ከዚያ የተለየ እንደሆነ ይገልጻል። *"... በሌላው ሰው መሠረት እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ሥፍራ ሳይሆን፥ ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ..."* ይላል (ሮሜ 15፥20)። ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተዘዋወረ አዳዲስ ሥራዎችን ይጀምር እንደነበረ እናውቃለን። በአንድ ሥፍራ ረጅም ጊዜ የቆየበት ሦስት ዓመት ሲሆን፥ ያም ኤፌሶን ውስጥ ነው (የሐዋ. 20፥31)።

የቀድሞ ሐዋርያት ይሠሩት የነበሩትን ሥራ ስንመረምር፥ በዘመናችን አንዳንድ አገልጋዮች፥ ሥራቸው (አገልግሎታቸው) ተመሳሳይነት እንዳለው እንገነዘባለን። አገልግሎታቸው የሚያተኩረው በአመኑትና ባላመኑት ላይ ከመሆኑም በላይ አዳዲስ ሥራዎችን የሚጀምሩ ናቸው። የወንጌል ተልዕኮ እንቅስቃሴን ይመሩ የነበሩትን፥ ለምሳሌ በመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ለአፍሪካ የሰበኩትን *ዴቪድ ሊቪንግስተን*፥ ለበርማ ተወላጆች የወንጌል መልዕክተኛ የነበሩትን *ጀድሰንን*፥ ወንጌልን ይዘው ወደ ሕንድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሄዱትን *ዊልያም ኬሪን*፥ ለቻይና ወንጌልን የሰበኩትን *ሀድሰን ቴይለርን* ሐዋርያት ብለው ይጠሯቸዋል። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ራዕይ ያላቸው አንዳንድ



የቤተ ክርስቲያናት መጋቢዎች መኖራቸው የታወቀ ነው። "የሐዋርያነት ስጦታ" ያላቸው ሰዎች ለረጅም ጊዜ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይቆዩም። አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት ከመሠረቱና ካደራጁ በኋላ፥ ሌላ አዲስ አገልግሎት ለመጀመር ወደ ሌላ ሥፍራ ይንቀሳቀሳሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ *"የሐዋርያነት"* ስጦታ እንዳላቸው ግልጽ ነው።

በተለይ በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ብዙ አዳዲስና እንግዳ ትምህርቶች እየገቡ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይናገራሉ። አሳሳቢ ከሆኑት ትምህርቶች መካከል አንደኛው ከላይ የገለጽነው "የሐዋርያት አገልግሎት" *(Apostolic Ministry)* ነው። የሐዋርያነትን ሹመት የሚሰጡና የሚቀበሉ ቢኖሩ፥ እምነታቸውና አሠራራቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው እንዳልሆነ ሊያውቁት ይገባል። *"የሐዋርያነት ስጦታ"* መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚሰጠው ስጦታ እንጂ፥ በሹመት የሚገኝ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይህ ጽሑፍ፥ በወቅቱ ያለውን ችግር ሙሉ በሙሉ ባይነካም፥ ወደፊት በሰፊው ለሚያዘጋጁት ጽሑፎች መንደርደሪያ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

☆ ☆ ☆ ☆

ምዕራፍ 13

# የእረኝነት ስጦታ

*"...እርሱም አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች... እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ" (ኤፌሶን4፥11)*

## 1. "የእረኝነት" አገልግሎት አዲስ አይደለም

በአንደኛው ክፍለ ዘመን የነበረችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ገና በመቋቋም ላይ ስለነበረች፥ መሪዎቿ አንዳንድ ችግሮች አልፎ አልፎ ያጋጥማቸው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በዚያን ዘመን ምዕመናኑን የሚያስተምሩበት በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጁ መንፈሳዊ መጽሐፍት እንኳን አልነበሯቸውም። ጳውሎስና እንዲሁም አንዳንድ ሐዋርያት ከጻፏአቸው ጥቂት ደብዳቤዎች በቀር፥ ወንጌሎቹ እንኳን በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅተው ገና አልቀረቡም ነበር። ይሁን እንጂ፥ መሪዎቹ ሕዝቡን ለአገልግሎት ማስታጠቅ (ማዘጋጀት) የሚያስችላቸውን ልዩ ዕውቀትና ኃይልን ከእግዚአብሔር ተቀብለው ነበር። ለሐዋርያት፥ ለነብያት፥ ለወንጌላውያን፥ ለመጋቢዎችና ለአስተማሪዎች መንፈስ ቅዱስ ልዩ ችሎታንና ዕውቀትን ሰጥቷቸው ነበር። *"ይህንንም ያደረገው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው"* (ኤፌ. 4፥12) ይላል።



የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና እንዲሁም በሐዋርያት የተጻፉ አንዳንድ መልዕክቶች፥ ለአገልግሎት የተመረጡ ሐዋርያት፣ ነብያት፣ ወንጌላውያን፣ እረኞችና አስተማሪዎች ልዩ ዕውቀትና ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተቀበሉ በመሆናቸው፥ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክ ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት በማድረግ፥ አማኞችን በእምነታቸው እንዲጸኑ በማበረታታት ከፍተኛ ትጋት ያሳዩ እንደ ነበር ይገልጻሉ። የእረኞችና የአስተማሪዎች ተቀዳሚ ኃላፊነት፥ ገና በመቋቋም ላይ ያሉትንና እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ትግል ያለባቸውን አዳዲስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ማበረታታትና ማጠናከር ነበር።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ *"የእረኝነት"* አገልግሎት ከነበራቸው ሐዋርያት መካከል ጎልቶ ይታይ የነበረው ጢሞቴዎስ እንደ ነበረ እናውቃለን። ጢሞቴዎስ በሄደበት ሥፍራ ሁሉ የእረኝነትን አገልግሎት ይፈጽም ነበር። አንድ ጊዜ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምእመናን መካከል አንዳንድ አሳፋሪ የሆነ ነገር መኖሩን ጳውሎስ ሲሰማ፥ የእረኛ ልብ የነበረውን ጢሞቴዎስን በአስቸኳይ ወደ ቆሮንቶስ ልኮት እንደነበረ እናስታውሳለን። *"በዚህ ምክንያት የተወደደውንና የታመነውን፥ በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፤ እኔ በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የማስተምረውንና በክርስቶስ ያገኘሁትን የአዲስ ሕይወት መመሪያ እርሱ ያሳስባችኋል"* (1 ቆሮ. 4፥17)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ

ፊልጵስዩስ ሊልከው አስቦ እንደነበረ ይናገራል። *"እኔ ስለ እናንተ ሁኔታ በመስማት እንድጽናና ጢሞቴዎስን በፍጥነት ወደ እናንተ ለመላክ እንደሚያስችለኝ በጌታ ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለ እናንተ ሁኔታ እንደ እኔ እየተጨነቀ የሚያስብ ከጢሞቴዎስ በቀር ሌላ ሰው የለኝም"* (ፊል. 2፥19-20)። በሌላ ጊዜ ደግሞ አማኞችን ከሐሰተኛ ትምህርት እንዲጠብቅ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ኤፌሶን ትቶ እርሱ ወደ መቄዶንያ እንደ ሄደ ለጢሞቴዎስ በላከው በመጀመሪያው ደብዳቤ ላይ ጠቅሶት እናነባለን። *"ወደ መቄዶንያ ስሄድ ሳለሁ አደራ እንዳልሁህ በኤፌሶን ተቀመጥ፤ እዚያ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርት እንዳያስተምሩና ወደ ተረትና መጨረሻ ወደሌለው ወደ ትውልዶች ቆጠራ እንዳይመለሱ እዘዛቸው"* አለው (1 ጢሞ. 1፥3-4)። ጢሞቴዎስ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት አንድ "እረኛ" ወይንም *መጋቢ* የሚፈጽመውን አገልግሎት እንደነበረ በግልጽ እናያለን።

በአንደኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች፥ አንድ የበግ "እረኛ" ከበጎቹ ጋር ያለው ግንኙነት፥ ለበጎቹ የሚያደርገው ጥንቃቄ ምን ዓይነት እንደሆነ ስለሚያውቁ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "እረኛ" ወይንም "*መጋቢ*" የሚለው አሳብ ወይንም ቋንቋ እንግዳ ነገር አይሆንባቸውም። እረኛው ለምዕመናኑ ያለበትን ኃላፊነት፥ እንዲሁም ለምዕመናኑ የሚሰጠው አገልግሎት ምን ዓይነት እንደሆነ ለመረዳት ይህን ያህል አይቸገሩም። በሃያኛው ክፍለ ዘመን ያለነው ክርስቲያኖች ግን፥ ብዙዎቻችን የከተማ ሰዎች በመሆናችን፥ የበግ እረኛ ከበጎቹ ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ በደንብ ስለማናውቅ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "እረኛ" የሚለው አሳብ፥ ወይንም ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ሆኖ ላይገባን ይችላል። "እረኛ" የሚለውን ቃል ሐዋርያው ጴጥሮስ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሁሉ የበለጠ ሲጠቀምበት እናያለን። *"በአደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ መንጋውን የምትጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዐይነት በፈቃደኝነት ይሁን፤ ለገንዘብ በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ፍላጎት ይሁን"* (1 ጴጥ. 5፥2)። እረኛ የበጎቹን ደህንነት የመጠበቅ፥ ከነጣቂ ተኩላዎች፥ ይኸውም ሐሰተኛ ከሆኑ አስተማሪዎች ምዕመናኑን የመከላከል ኃላፊነት አለበት (የሐዋ. 20፥28-29)። የእግዚአብሔርን አሳብ በመግለጽ "በቃሉ እውነት" በጎቹን ማሳደግ እንዳለበት እናውቃለን (ቲቶ 1፥9)።



## 2. ሁለት ዓይነት "እረኞች" አሉ

በዘመናችን ሁለት ዓይነት የቤተ ክርስቲያን "እረኞች" (ፓስተሮች) እንዳሉ እንገነዘባለን። እነርሱም፥ የእረኝነት "ስጦታ" ያላቸውና እንዲሁም የእረኝነት "ሥልጣን" (ቦታ) የያዙ ናቸው።

### 2.1. "የእረኝነት ስጦታ" ያላቸው እረኞች

በዘመናችን "የቤተ ክርስቲያን እረኛ" ወይንም "መጋቢ" እየተባለ የሚጠራው፥ የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪ በመሆን የሚያገለግለው ሰው ነው። በአገልግሎታቸው የተሳካላቸው የሚመስሉት የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች (ፓስተሮች)፥ ሁሉም *"የእረኝነት ስጦታ"* አላቸው ማለት አይደለም። ብዙ ምዕመናን ያሏቸው የትላልቅ ቤተ ክርስቲያናት መጋቢዎች (ፖስተሮች) አብዛኞዎቹ "የእረኝነት ስጦታ ያላቸው አይደሉም።

*"የእረኝነት ስጦታ"* ማለት ምንድነው? *ፒተር ዋግነር* "የእረኝነት" ስጦታ ምን እንደሆነ ሲገልጹ፥ *"እግዚአብሔር ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚሰጠው ልዩ ችሎታ ነው፤ ያም ችሎታ ለረጅም ጊዜ ለአንድ "ማኅበረ-ምዕመናን" መንፈሳዊ ደህንነትና ዕድገት ሙሉ ጥንቃቄ ማድረግ ነው"* ይላሉ። መጋቢ ወይንም እረኛ ተብሎ የሚጠራው ሰው፥ *ዋና እረኛ* በሆነው ክርስቶስ *ሥር* ሆኖ፥ *የሚያስተምር፣ የሚመግብ፣*

ቁስላቸውን የሚፈውስ፣ አንድነታቸውን የሚጠብቅ፣ "ማኅበረ-ምዕመናኑን" በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የአገልግሎት ስጦታቸውን እንዲያውቁ የሚያደርግ፣ በእምነታቸው፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚያደርጋቸውን ሥራ ሁሉ የሚሠራ፣ ለአገልግሎት የሚያዘጋጅ ወይንም የሚያስታጥቅ ሰው ነው። "የእረኝነት ስጦታና" እንዲሁም "የእረኝነትን ቦታ" ወይንም ማዕረግ ይዞ ማገልገል፥ ሁለቱ አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ማወቅ አለብን። ስለዚህ መጋቢ፥ ወይንም ፓስተር የሆኑ ሁሉ የመጋቢነት ስጦታ ያላቸው እንዳልሆኑ እንረዳለን። በአገራችን መጋቢ (ፓስተር) የሚለው አሳብ አዲስ ሲሆን፥ በሌላው ዓለም ግን በጣም የተለመደና "መጽሐፍ ቅዱሳዊ" የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። በአሜሪካ የምናያቸው መጋቢዎች (ፓስተሮች) አብዛኛዎቹ ስጦታው ሳይኖራቸው "የመጋቢነት ቦታ" የያዙ እንደሆኑ እንገምታለን። ከአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ ደሞዝ እየተከፈላቸው የሚሠሩ፥ የሙሉ ጊዜ ቅጥር ሠራተኞች ብቻ ናቸው። ፓስተር ሆነው እንዲያገለግሉ ሲቀጠሩ፥ "ስጦታው" አላቸው ተብለው፥ ተረጋግጦላቸው አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ የመጋቢነት ስጦታው እያላቸው መጋቢዎች ያልሆኑ፥ ወይንም በሌላ ዓይነት አገልግሎት ውስጥ ተሰልፈው የሚያገለግሉ አንዳንድ አማኞች እንዳሉ ማወቅ ያስፈልገናል። "ማኅበረ-ምዕመናኑ" እውነተኛ መንፈሳዊነት ሲኖረው፥ የእነዚህን አማኞች የጸጋ ስጦታ ለይቶ ማወቅ ይችላል።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፥ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን የጀመረውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋት ሥራ መቀጠል እንዳለባት እናውቃለን። ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነቷን መፈጸም እንድትችል፥ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ስጦታን በመስጠት ያዘጋጃታል። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የአገልግሎት ክፍሎች ሲገልጽ፥ *"...አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ ነቢያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ*



*ስጦታዎችን ሰጠ"* ይላል (ኤፌ. 4፥11)። "እረኛ" የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ *"መከላከል፥ መጠንቀቅ"* ማለት ነው። ከላይ ያየነውን ጥቅስ የበለጠ ለመረዳት፥ *"ስጦታና"* (gift) *"የአገልግሎት ሥልጣንን"* (office) ለይተን ማየት አስፈላጊ ነው። በኤፌሶን 4፥11 ላይ የተዘረዘሩትን፥ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ስጦታ የሰጣቸውን አምስት ዓይነት መሪዎችን እናያለን። እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያላቸው መሪዎች የተሰጡት ለዓለም፥ ወይንም ለራሳቸው ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ነው።

"የመጋቢነት ሥልጣን" የተሰጠው ሰው፥ ለምዕመናኑ የመጠንቀቅ ኃላፊነት እንዳለበት ብቻ ሳይሆን፥ በምዕመናኑ ላይም ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ማወቅ ይገባናል። ሥልጣን እንደተሰጠው አውቀን ማክበርና መቀበል ካልቻልን፥ አገልግሎቱን እንደሚገባው መፈጸም አይችልም። "ሥልጣን" ስንል፥ "የአንድ ሰው አምባ ገነን የሆነ አገዛዝ" *(autocracy)* ማለታችን አይደለም። ይህን ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት እንዳይኖር ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ኛ መልዕክቱ ላይ ጥሩ የሆነ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። *"በዐደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ መንጋውን የምትጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዐይነት፥ በፈቃደኝነት ይሁን፤ ለገንዘብ በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ፍላጎት ይሁን። እንዲሁም በእናንተ ኃላፊነት ሥር ያሉትን ጨቁኖ በመግዛት ሳይሆን ለመንጋው መልካም ምሳሌነትን በማሳየት ይሁን"* ይላል (1ኛ ጴጥ. 5፥2-3)።

የሥነ መለኮት ምሑር የሆኑት *ፎልክስ* የተባሉት ሰው የአምስቱ የአገልግሎት ሥጦታዎችን ተግባራቸውን ሲጠቅሱ፥ *"ሐዋርያትና ወንጌላውያን አገልግሎታቸው በየሥፍራው እየዞሩ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ሲሆን፥ ነቢያት ደግሞ፥ ከእግዚአብሔር ለተለየ ጊዜ የሚያስተላልፈውን መልዕ*

*ከት ተቀብለው ለሕዝቡ የሚሰጡ ናቸው። እረኞችና አስተማሪዎች ደግሞ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በየቀኑ የሚያሳድጉና የሚያንጹ ናቸው”* አሉ። “የእረኝነትን” ስጦታንና ተግባር የበለጠ ለመረዳት፥ በበግና በእረኛው መካከል ያለውን ግንኙነት ማወቅ ይጠቅማል። እረኛው በጎቹን ከውስጥም ሆነ ከውጪ ለማጥቃት ከሚመጣ ጠላት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት። ሥራው በጎቹን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ ማስተማር፣ መምራት፣ መመገብ፣ ሕይወታቸው የሚታደስበትን የእረፍት ጊዜን ማዘጋጀትንም ያጠቃልላል። የጠፉትን መፈለግ፣ የባዘኑትን መመለስ፣ የቆሰሉትንና የተጎዱትን ቁስላቸውን መጠገን፣ ከመንጋው ጋር ሕብረት እንዲኖራቸው ማድረግ ተጨማሪ ሥራው ነው። ሁል ጊዜ ምዕመናኑ ከእርሱ እየጠበቁ፥ ራሳቸውን እያፋፉ እንዲኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ ለአገልግሎትም ማዘጋጀት አለበት። *“...የክርስቶስ አካል የሆንችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው”* ይላል (ኤፌ. 4፥12)። እረኛው፥ ማኅበረ ምዕመናኑ አንዱ ሌላውን እንዲያገለግል፥ ያሉበትን የአጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲያጸኑ ማስታጠቅ ይኖርበታል። በኤፌሶን 4፥11 ላይ ከተዘረዘሩት “የአገልግሎት ሥልጣኖች” መካከል ሦስቱ፥ ይኸውም “ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አገልግሎታቸው ለዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፥ ሁለቱ ማለትም “እረኞችና አስተማሪዎች” ግን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። በአንደኛው ክፍለ ዘመን ሆን ተብሎ ይህን ዓይነት ክፍልፍል ተሰጥቷል ማለት አይደለም። በእኛ ዘመን ግን ከላይ በገለጽነው ዓይነት የተከፋፈለ መሆኑን እናውቃለን።

*“የእረኝነት ስጦታ”* ማኅበረ-ምዕመናኑን ከማስተማር ያለፈ ነው። ትልቅ ትዕግሥትን የሚጠይቅ፥ በተወሰነ ጊዜ የማያልቅ የረጅም ጊዜ አገልግሎት ነው። እረኛው የማስተማር ስጦታ



ሲኖረው፥ “የእረኛነት” አገልግሎቱን የበለጠ ሊያጠናክርለት ይችላል። ብዙ ጊዜ “እከሌ ጥሩ ሰባኪ ነው፤ ግን ጥሩ እረኛ (መጋቢ) አይደለም”፥ ወይንም “ጥሩ እረኛ ነው፤ ግን ጥሩ ሰባኪ አይደለም” የሚለውን አስተያየት እንሰማለን። ይህን ዓይነት አስተያየት የምንሰጠው “እረኝነትና ማስተማር” ሁለት የተለያዩ ስጦታዎች መሆናቸውን ዘንግተን፥ ልክ እንደ አንድ “ስጦታ” አድርገን በመመልከት ይሆን? አንድ አማኝ ከአንድ ስጦታ በላይ ሊኖረው ስለሚችል፥ ብዙ ጊዜ *“የእረኝነት ስጦታ”* ያለው ሰው፥ *“የማስተማርም ስጦታ”* እንደተሰጠው እናያለን። ይሁን እንጂ፥ “የማስተማር ስጦታ” የሌለው ሰው፥ “የቤተ ክርስቲያን እረኛ” መሆን አይችልም ወይ? ብለን *መጠየቃችን አይቀርም።*

ለዚህ ጥያቄ ሁለት የተለያዩ መልሶች (አስተያየቶች) እናገኛለን። የመጀመሪያው፥ “የማስተማር ስጦታ” ከሌለው “የቤተ ክርስቲያን እረኛ” መሆን አይችልም የሚል አቋም ያላቸው ክፍሎች የሚሰጡት መልስ ነው። ይህን የሚሉበት የራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው። ይኸውም፥ “የቤተ ክርስቲያን እረኛ” ትልቁ ሥራው “ማስተማር” ወይንም ምዕመናኑን መመገብ ስለሆነ፥ ማስተማር ካልቻለ ምዕመናኑን ጤናማ መንፈሳዊ ምግብ እየመገበ ማሳደግ አይችልም ይላሉ። ሁለተኛው፥ “የማስተማር ስጦታ” ባይኖረውም፥ “የቤተ ክርስቲያን እረኛ” መሆን ይችላል የሚል አቋም ያላቸው ክፍሎች ናቸው። “የቤተ ክርስቲያን መጋቢ”፥ ኃላፊነቱ ምዕመናኑን መመገብ ብቻ ሳይሆን፥ *የጠፉትን መፈለግ፥ የባዘኑትን መመለስ፥ የቆሰሉትንና የተጎዱትን ቁስላቸውን መጠገንና፥* እንዲሁም ሌሎች ሥራዎችን መፈጸም ስለሆነ፥ ማስተማርም ባይችልም፥ የእረኛነት ልብ ካለው፥ “የቤተ ክርስቲያን እረኛ” መሆን ይችላል። “በኅብረት አገልግሎት” *(team ministry)* የሚያምን ከሆነ፥ እርሱ ሌሎቹን ሥራዎች ሲፈጽም፥ “የማስተማር ስጦታ” ያለው ሌላ ሰው የማ

ስተማሩን ኃላፊነት መውሰድ ይችላል" ይላሉ። በበኩሌ ይሄኛውን አቋም የመደገፍ ዝንባሌ ቢኖረኝም፣ በውስጤ አንዳንድ ጥያቄዎች ሳይፈጠሩ አይደለም። የትኛው የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነው፣ "እኔ የማስተማር ስጦታ የለኝም፤ እከሌ ከእኔ የበለጠ ጥሩ አድርጎ ያስተምራል፤ ምዕመናኑም እርሱ ሲያስተምር የበለጠ ይባረካሉ፤ የበለጠ ይማራሉ፤ ስለዚህ እኔ ልቀመጥና እርሱ ያስተምር" በማለት ምንም ቅር ሳይለው የማስተማር ኃላፊነቱን ለሌላው መስጠት የሚችል? ዛሬ ያለስጦታቸው "የእረኝነትን" ሥልጣን በተለያየ ምክንያትና ዘዴ ይዘው፣ የማስተማር ሥጦታም ሆነ ችሎታ ሳይኖራቸው "እናስተምራለን" በማለት ምዕመናኖቻቸውን አረፋ የሚመግቡ፣ ጥቂቶች እንዳልሆኑ እናውቃለን። በምዕመናን ሕይወት ውስጥ "መንፈሳዊ መቀጨጭ" የሚታይበት ትልቁ ምክንያት፣ የበሰለ መንፈሳዊ ምግብ በማጣት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን።

"የቤተ ክርስቲያን እረኛ" ወይንም "መጋቢ" የሆኑ ሰዎች አገልግሎታቸው፣ ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት፣ እንድትታነጽና ራሷን እንድታባዛ ማድረግ ነው። እርግጥ ነው በእረኝነት ደረጃ የተቀመጡ ሰዎች፣ "የማስተማር" አገልግሎት መስጠት እንደሚጠበቅባቸው የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፣ የእረኛነት ስጦታ ያለው ሁሉ "የማስተማርም" ስጦታ ይኖረዋል ማለት እንዳልሆነ ተመልክተናል። ማስተማር ከእረኛው አገልግሎት ጋር ይያያዝ እንጂ፣ የእረኛው አገልግሎት በጎቹን መምራት፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አደጋ እንዳይደርስባቸው መጠንቀቅን ያጠቃልላል። "የእረኝነት ስጦታ" በኢትዮጵያውያን መካከል ተለይቶ ብዙ የታወቀ ባይሆንም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ ሲሄድ በማየታችን፣ እንዲሁም አንዳንድ ወጣቶች ራሳቸውን የበለጠ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት የመለኮት ትምህርት ሲከታተሉ ማየታችን በጣም ደስ አሰኝቶናል።



## 2.2. "የእረኛነት" ቦታ (ሥልጣን) የያዙ እረኞች

*"የእረኝነት ስጦታ"* ሳይኖራቸው በተለያየ ምክንያት አገልግሎት ውስጥ ገብተው ቀስ በቀስ "የእረኛነት" ቦታ (ሥልጣን) ላይ የመቀመጥ ዕድል ያጋጠማቸው አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ሁለቱም ዓይነት "የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች" (ፓስተሮች) በአገልግሎታቸው የተለያየ ፍሬ ወይንም ውጤት ያሳያሉ። ስጦታው ሳይኖራቸው "የመጋቢነትን" ሥልጣን የያዙ፣ ቤተ ክርስቲያናቸው በቁጥር አይጨምርም ወይንም አያድግም ማለት አይደለም። አንዳንዶቹ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያን ያላቸው ናቸው። የትላልቅ ቤተ ክርስቲያን እረኛ (መጋቢ) ስለሆኑ ብቻ፣ "የእረኛነት ስጦታ" አላቸው ማለት አይደለም። እንዲሁም የትናንሽ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች (ፓስተሮች) የሆኑት ደግሞ *"የእረኝነት ስጦታ"* የላቸውም ማለት አይደለም። ብዙዎቻችን የአገልግሎትን ፍሬያማነት "በማኅበረ-ምዕመናን" ቁጥር መብዛትና ማነስ የመለካት ዝንባሌ አለን። ይሄ ትልቅ ስህተት ነው። ብዙ አባሎች ያሉት "ጥሩ መጋቢ"፣ ብዙ አባሎች የሌሉት ደግሞ፣ "ደካማ መጋቢ" ማለት ትክክለኛ አስተያየት አይደለም። ጥቂት አባሎች ያላቸው አንዳንድ መጋቢዎች፣ ብዙ አባሎች ካላቸው መጋቢዎች በስብከት፣ በማስተማር፣ በአስተዳደር ችሎታ እንዲሁም በብዙ አቅጣጫ የተሻሉ እንደሆኑ አንጠራጠርም።

ያለስጦታቸው "በእረኝነት" የሚያገለግሉ አማኞች ፍሬያማ ካለመሆናቸውም ሌላ፣ ጥሩ ደሞዝ ቢያገኙም፣ ያለቦታቸው እንደተቀመጡ ስለሚያውቁ በሕይወታቸው ብዙ ጊዜ ደስተኞች አይደሉም። ወደ አገልግሎት የገቡት እግዚአብሔር በመጋቢነት እንዲያገለግሉ መርጧቸው ሳይሆን፣ የአገልግሎት በር ስለተከፈተላቸው፣ በወቅቱ ሌላ ምርጫ ስላልነበራቸው፣ ወይንም ለሌላ ሥራ የሚያበቃ ትምህርትም ሆነ አስፈላጊው የሥራ ልምምድ ስለሌላቸው፣ ወይንም ቀላል ሆኖ ያገኙት "የመጋቢነት

ሥራ" በመሆኑ ብቻ ወደ አገልግሎት የገቡ እንደሆነ ሌላ ሰው ባያውቅ እነርሱ ራሳቸው ያውቃሉ። ለራሳቸው እውነተኞች ከሆኑ፣ "የተቀመጥኩት ያለቦታዬ፣ ያለጥሪዬ፣ ወይንም ያለስጦታዬ ነው" እንደሚሉ እናምናለን። ይሁን እንጂ፣ አብዛኞዎቹ ወደ አገልግሎት ለምን እንደገቡ እውነቱን አይናገሩም። "እግዚአብሔር ጠርቶኛል" በማለት ሽንጣቸውን ገትረው እንደሚከራከሩ አንጠራጠርም። ስጦታው ሳይኖራቸው "በእረኝነት" ቦታ የተቀመጡ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን "እረኞች"፣ ሌላው ቀርቶ የእረኛነት ወይንም የመጋቢነት ስጦታና አገልግሎት ምን እንደሆነ በደንብ የሚያውቁት አይመስለንም። በዚህ ምክንያት የሕዝቡ አገልጋይ (አሽከር) በመሆን ፈንታ የሕዝቡ "ጌታ"፣ ለአገልግሎት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በመስጠት ፈንታ ሕዝቡን አስጨንቀው የሚገዙ "አምባ ገነኖች" (ዲክቴተሮች) ሲሆኑ ይታያሉ።

"የእረኛ" አገልግሎት ምን እንደሆነ ያልገባቸው አገልጋዮች ብቻ ሳይሆኑ፣ እንዲያገለግሏቸው የሚጠሯቸው፣ ወይንም የሚቀጥሯቸው "ማኅበረ ምዕመናንም" አብዛኞዎቹ የገባቸው አይመስሉም። በዚህ ምክንያት አንዳንዶቹ መጋቢዎቻቸውን እንደ ትናንሽ አምላኮች በመቁጠር፣ ሲያመልኳቸው ይታያሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ መጋቢዎቻቸውን እንደ ተላላኪ ወይንም እንደ "ጨሎ" ሊያዟቸው የሚሞክሩ እንዳሉ እናውቃለን። በዚህ ምክንያት በእረኛውና በሕዝቡ መካከል ከፍተኛ አለመግባባት ይፈጠራል። አለመግባባቱ እየጠነከረ ሲሄድ ለቤተ ክርስቲያን መከፈል ምክንያት ይሆናል። "መጋቢ ያስፈልገናል" ብለው መጋቢውን የሚደግፉና፣ "መጋቢ አያስፈልገንም" በሚሉት መካከል ከፍተኛ ግጭት ይፈጠርና ቤተ ክርስቲያኑ ለሁለት ይከፈላል። በዚህ ዓይነት መጥፎ ልምምድ ውስጥ ያለፉ ማህበረ ምዕመናን፣ "ሁለተኛ መጋቢ አያስፈልገንም" በማለት ውሳኔ ያስተላልፋሉ።



አንድ የቤተ ክርስቲያን እረኛ (መጋቢ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አገልግሎት ምን እንደሆነ በተለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል በደንብ የታወቀ አይመስልም። "እረኛ አያስፈልገንምI መመራት የምንፈልገው በሽማግሌዎች ቦርድ ነው" የሚሉት ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። እኔ በአገልግሎቴ "የቤተ ክርስቲያን እረኛ" (ፓስተር) ስላልሆንኩ፣ ለራሴ ብዬ ስለማልከራከር፣ በመጋቢነት ከሚያገለግሉ ወንድሞች ይበልጥ፣ በዚህ ነጥብ ላይ የሚሰማኝን በግልጽ ለመናገር ሙሉ ድፍረት አለኝ። ለቤተ ክርስቲያን በዘመናችን "መጋቢ" (ፓስተር) ያስፈልገናል ወይ? አስፈላጊስ ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው አገልግሎት፣ ኃላፊነቱና ሥልጣኑ ምንድነው? ከዚህ በፊት አንዳንድ "አምባገነን" የሆኑ፣ ጥሪውና ስጦታው ሳይኖራቸው የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ሆነው ስላበላሹ ብቻ፣ "የእረኝነትን አገልግሎት" ወይንም ስጦታን ከቤተ ክርስቲያን ሰርዞን ማውጣት ትክክል ነው ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

የቤተ ክርስቲያን እረኛ (መጋቢ) የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ቃሉን እያስተማረ ጤናማ ሆነው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚረዳ፣ ምዕመናኑን ለአገልግሎት የሚያበቃ (የሚያስታጥቅ) አገልጋይ እንደሆነ አይተናል። በዘመናችን የምናያቸው "መጋቢዎች" እውነተኛ የሆነውን፣ ከላይ የገለጽነውን ዓይነት "የእረኝነት አገልግሎት" ይፈጽማሉ ወይ? ለዚህ ጥያቄ የተለያየ መልስ እንደምናገኝ እርግጠኞች ነን።

### 3. አንዳንዶች "እረኛ (መጋቢ) አያስፈልግም" የሚሉበት ምክንያት ምን ይሆን?

3.1. "እረኛ" (መጋቢ) ካለ፣ ሥልጣኑ በብዙዎች እጅ በመሆን ፈንታ፣ የአንድ ሰው አመራር ወይንም ሥልጣን ይሆንና፣

መጋቢው "እኔ ቆራጭና ፈላጭ ነኝ፤ ማብሪያና ማጥፌ
ያው በእኔ እጅ ይሁን ይላል" በማለት "የእረኛነትን አገል
ግሎት" መቀበል የሚያቅታቸው አማኞች አሉ። በዘመና
ችን "አምባ ገነን" የሆኑ መጋቢዎች የሉም ማለት አንች
ልም። ብዙ አሉ። "እግዚአብሔር ራዕይን ለቤተ ክርስቲ
ያን የሚሰጠው በእኔ በኩል ብቻ ነው" የሚሉ፥ የእነር
ሱን ፈቃድ ብቻ ይፈጽማሉ ብለው የሚገምቷቸውን ሰዎች
ብቻ በሽማግሌነት የሚሾሙ፥ ከእነርሱ ጋር የማይስማማ
አስተያየት ያላቸውን፥ "ለምን እንዲህ ይሆናል?" ብለው
የሚጠይቋቸውን ሽማግሌዎች የሚሽሩ፣ እጃቸውን በሁሉም
ነገር ውስጥ የሚከቱ፣ ዘማሪ፥ ዲያቆን፣ ገንዘብ ያዥ
መሆን የሚያምራቸው፣ ለማንም ተጠያቂ አይደለሁም
የሚሉ፣ ምዕመናኖቻቸውን በአገልግሎት የማያሳድጉ፣ አን
ዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች እንዳሉ አንጠራጠ
ርም። እንዲህ ዓይነቶቹ ብዙዎቹ "የእረኝነት" ጥሪ፥ ወይ
ንም ስጦታው ሳይኖራቸው፥ ለደሞዙ ሲሉ ብቻ የገቡ
እንደሆኑ ግልጽ ነው። መጋቢ የሆነ ሁሉ ይህንን ዓይነት
አቋም ካለው፥ በእርግጥ አስፈላጊነቱ ሊያጠራጥረን ይች
ላል። ይሁን እንጂ፥ አንዳንዶቹ እረኛ ሳይሆኑ፥ "እረኛ
ነን" ብለው ስላበላሹ ብቻ፥ አንዳንዶቹ አምባ ገነን ስለ
ሆኑ ብቻ "እረኛ ፈጽሞ አያስፈልግም" ማለት እግዚአብ
ሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን የጸጋ ስጦታ ማቃለል
ወይንም ችላ ማለት ይሆናል ብዬ እፈራለሁ።

3.2. "መጋቢ ካለ፥ አገልጋዩ እርሱ ብቻ ይሆናል፤ ሌሎች የማ
ገልገል ዕድል አይኖራቸውም" ብለው በማሰብ "የመጋቢ
ነትን አገልግሎት" መቀበል የሚያቅታቸው አሉ። ይህ
ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉን
ነገር የማድረግ አቅምና ችሎታ ያለው የለም። የእረኛው



ትልቁ፥ ወይንም ዋናው አገልግሎቱ ምዕመናኑን መንፈ
ሳዊ ምግብ መመገብ እንደሆነ እርግጠኞች ነን። ስለሆነም
መጋቢው ይሰብካል፤ ያስተምራል። ከመስበክና ከማስተማር
ሌላ ደግሞ የማስተዳደር ስጦታ ካለው፥ ያስተዳድራል፤
ከሌለው ግን ስጦታው ባላቸው ሰዎች ይጠቀማል። "በዚህ
አቅጣጫ ደካማ ነኝ" ብሎ የሌሎችን ሰዎች ድጋፍ መፈ
ለግ ደካማነት መስሎ ሊሰማው አይገባም። መጋቢው
"በሁሉም ነገር ብቃት አለኝ" ብሎ ቢያስብ፥ ራሱን ያታ
ልላል። እንደ እግዚአብሔር ቃል እያንዳንዱ የቤተ ክርስ
ቲያን አባል፥ የአገልግሎት ድርሻ ሊኖረው ያስፈልጋል።
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ የአገልግሎት ዘርፎች አሉ።
አገልግሎት ሲባል፥ መስበክ ወይንም ማስተማር ብቻ
የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ፥ በአምልኮ
መምራት፣ በመዘምራን ጓድ ውስጥ ማገልገል፣ የሙዚቃ
መሣሪያ መጫወት፣ የሰንበት ትምህርት ማስተማር፥ የመ
ጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምራት፣ በድራማ፣ በልዩ ልዩ
የጉልበት ሥራ፣ በጸሎት፣ በግላዊ የወንጌል ሥርጭት፣
በመዋዕለ ሕጻናት፣ በአስተናጋጅነት፣ ድሆችን በመርዳት፣
በአስተዳደር፣ በሂሳብ ሥራ፣ በጸሐፊነትና በመሳሰሉት
አገልግሎቶች ውስጥ ሁሉ ምዕመናን እየገቡ ማገልገል
ይችላሉ።

የክርስቶስ አካል ማደግ የምትችለው፥ እያንዳንዱ ብልት
ስጦታው ምን እንደሆነ አውቆ አገልግሎቱን በአግባቡ
መፈጸም የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው። በአካል ውስጥ የተለ
ያየ አገልግሎት ያላቸው የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንዳሉ
ሁሉ፥ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ አማኞች የተለያየ አገል
ግሎት አላቸው። የሁሉም አገልግሎት ካልተመሳሰለ በክ
ርስቶስ አካል ውስጥ ሥፍራ የላቸውም ማለት አይደለም።

ስለዚህ "መጋቢው" እውነተኛ ከሆነ ምዕመናኑ የበለጠ የአገልግሎት ሥጦታቸውን እንዲያውቁ፥ ለአገልግሎት የበለጠ እንዲዘጋጁ ያደርጋል እንጂ፥ እነርሱን ተመልካች አድርጎ እርሱ ብቻ አገልጋይ አይሆንም። አንዳንድ ሰዎች የመጋቢን መኖር የሚቃወሙት፥ አገልግሎት ሲባል መስበክ ወይንም ማስተማር ብቻ ስለሚመስላቸው፥ መጋቢ ወይንም ፓስተር ከመጣ፥ እንደ ዕቁብ በየተራ ሁሉም መስበኩ ይቀራል ብለው ስለሚፈሩ ነው። ይህ እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክለኛ ፍርሃት አይደለም። ይህን ስንል ደግሞ "ከፓስተሩ" በስተቀር ሌላ ሰው በፍጹም መስበክ የለበትም ማለታችን እንዳልሆነ ይታወቅ።

3.3. "መጋቢ አያስፈልግም" የሚሉት አንዳንድ ሰዎች ፍርሃታቸው፥ የማስተማር፣ የመስበክና የመምራት ችሎታ ያለው፣ ለዚህ አገልግሎት ብቃት ያለው፣ ሙሉ ጊዜውን ለአገልግሎት የሰጠ ሰው አይገኝም በማለት ይመስላል። ማንኛውም ሰው፥ በየትኛውም የሥራ መስክ ለመሰለፍ፥ አስፈላጊውን የትምህርት ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት እናውቃለን። ለምሳሌ፥ "ኢንጂነር" ወይንም መሀንዲስ ለመሆን የሚፈልግ ሰው፥ ለመሀንዲስነት እንዲበቃ ቢያንስ ቢያንስ አስራ ስድስት ዓመት ትምህርት ቤት ገብቶ መማር አለበት። ከመሀንዲሶች ጋር በመዋል ብቻ "መሀንዲስ ነኝ" ቢል፥ በብዙ ሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ አደጋና ችግር ያደርሳል። በመሀንዲስነት ተቀባይነት የሚያገኘው፥ ለዚያ የሚያበቃውን ፈተና ሲያልፍ ብቻ ነው። ሀኪም ለመሆን የሚፈልግም ሰው፥ ቢያንስ ቢያንስ ሃያ ዓመት ትምህርት ቤት መቆየት ያስፈልገዋል። ሃያ ዓመት ትምህርት ቤት መቆየት ብቻ ሳይሆን፥ የሚማረውን ለማወቅ ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረግ አለበት። ማናችንም ብንሆን፥ በቂ ዝግጅት የሌለው፥ በሕክምና ዓለም



ውስጥ በቂ ልምምድ ያላገኘ፥ ያልተመሰከረለት፥ ራሱን "ሀኪም" ብሎ የሚጠራ ሰው፥ የቀዶ ጥገና እንዲያደርግልን ራሳችንን አሳልፈን እንደማንሰጥ ግልጽ ነው።

የምድራዊው ነገር ይህን ያህል ዝግጅት ከጠየቀ፥ መንፈሳዊውና፥ ዘላለማዊ የሆነውማ ምን ያህል ከፍተኛ ዝግጅት ይጠይቅ ይሆን? "መጋቢ" ሆኖ የሚያገለግለው ሰው፥ ኀላፊነቱ ስለ ሰዎች "ነፍስ" ጉዳይ መጨነቅ ነው። ችሎታ የሌለው፥ በቂ ዝግጅት ያላደረገ ሀኪም በሰዎች አካል ላይ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችለው ሁሉ፥ በቂ ዝግጅት የሌለው "መጋቢ" ሰዎች የሚድኑበትን መንገድ በመዘርጋት ፈንታ ወደ ጥፋት ሊገፋ እንደሚችል ግልጽ ነው። ጌታን ለማገልገል ዕውቀት ሳይሆን ድንቁርና የሚያስፈልግ የሚመስላቸው "ወግ አጥባቂ ክርስቲያኖች" በየቦታው እንዳሉ እናውቃለን። ስንፍናቸውን የበለጠ መንፈሳዊ መልክ ለመስጠት፥ "በመንፈስ እንጂ በዕውቀት አይደለም" በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ያለአግባብ በመተርጎም ድካማቸውን ለመሸፈን ይሞክራሉ። በሰለጠነው ዓለም "መጋቢዎች" እንደማንኛውም የሥራ መስክ፥ ለመንፈሳዊ አገልግሎታቸው በቂ የትምህርት ዝግጅት ያደርጋሉ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመጨረስ 12 ዓመት፥ ኮሌጅ 4 ዓመት፥ የመለኮት ትምህርት ለመማር 3 ዓመት፥ በጠቅላላው 19 ዓመት ትምህርት ቤት ያሳልፋሉ። አሜሪካን አገር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶች በየዓመቱ ትምህርታቸውን እየጨረሱ በመጋቢነት፥ በአስተማሪነት፥ እንዲሁም በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ይሰለፋሉ።

እኛም ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት፥ ጥሪ ያላቸው፥ ራሳቸውን በትምህርት ያዘጋጁ መጋቢዎች፥ አስተማሪዎች፥ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ እየገቡ የሚያገለግሉ ሰዎች ያስፈልጉናል። የህክምና ሙያ ያለው ሰው ባለመኖሩ

ብቻ "የህክምና ሙያ" የለም ማለት ትክክል አይመስለኝም። ልክ እንደዚሁ "የመጋቢነት" ችሎታ ያላቸው ሰዎች ስለሌሉ፥ ወይንም ጥሪያቸውንና ስጦታቸውን ለይተው ባለማወቃቸው ብቻ፥ "የመጋቢነት አገልግሎት" ወይንም ስጦታ የለም፥ ወይንም በሌላ ነገር እንተካው ማለት ልክ አይመስለኝም። በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ ወጣቶች ራሳቸውን የበለጠ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት፥ የመለኮት ትምህርት በመማራቸው ብዙዎቻችንን ደስ እያሰኘን ነው። ወደ አገልግሎት መግባት ያለባቸው ከትምህርት ቤት የወደቁ፥ ወይንም ሌላ ትምህርት መማር ስለማይችሉ ብቻ የመለኮት ትምህርት እየተማሩ ወደ አገልግሎት የሚሰማሩ ሰዎች ብቻ መሆን የለባቸውም። በቂ ዕውቀት ያላቸው፥ አዕምሮአቸው ትምህርት የሚቀበልላቸው ጎበዝ የሆኑ ሰዎች ወደ አገልግሎት ጌታ እንዲጠራ መጸለይ ይገባናል። ሳይማሩ ማገልገል አይቻልም ማለቴ ሳይሆን፥ በስጦታችን ላይ ትምህርት ቢጨመርበት አገልግሎታችንን የበለጠ ያሳድገዋል ማለቴ ነው። የቀድሞ ሐዋርያት የቀለም ትምህርት አይኑራቸው እንጂ፥ በክርስቶስ እግር ሥር ሦስት ዓመት ተኩል የተማሩ መሆናቸውን እናውቃለን። ድንቁርና እርግማን እንጂ፥ በረከት እንዳልሆነ እናውቃለን። ተምሮ የቃሉን ምስጢር መመርመር ደካማነት አይደለም። *"በቤርያ ያሉት አይሁዳውያን በተሰሎንቄ ካሉት ይልቅ ቅን አመለካከት ያላቸው ስለነበሩ ቃሉን በታላቅ ደስታ ተቀበሉ፤ የቃሉንም እውነተኛነት ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጽሐፍትን ይመረምሩ ነበር"* (የሐዋ. 17፥11)።

## 4. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሽማግሌዎች ብቻ ብትመራስ?

*"እንግዲህ እኔ ከእነርሱ ጋር አብሬ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የሆንሁ፥ የክርስቶስም መከራ ምስክር የሆንሁ፥ እንዲሁም ወደፊት የሚገለጠው ክብር ተካፋይ የምሆን፥ በመካከላችሁ*



*ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ። በአደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ መንጋውን የምትጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዓይነት በፈቃደኝነት ይሁን፤ ለገንዘብ በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ፍላጎት ይሁን"* (1ኛ ጴጥ. 5፥1-2)

በሐዋርያት ዘመን፥ አንዲት የአጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ከአንድ ሰው በላይ በሆኑ መሪዎች ትመራ እንደነበረ ከላይ ባነበብነው መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መረዳት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ሽማግሌ" የሚለው ቃል በነጠላ ሳይሆን ሁልጊዜ በብዙሃን፥ ማለትም "ሽማግሌዎች" በማለት ሲጠቀስ እናነባለን። በነጠላ የተጠቀሰው አራት ጊዜ ብቻ ነው (1 ጢሞ. 3፥2፣ ቲቶ 1፥7፣ 2ኛ ዮሐ. ቁ. 1፣ 3ኛ ዮሐ. ቁ. 1)። ከላይ ባነበብነው ጥቅስ መሠረት መንጋውን የሚጠብቀው በዘመናችን እንደምናየው አንድ "እረኛ" (መጋቢ) ብቻ አልነበረም። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አንድ መሪ ብቻ አናይም፥

> *"የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችንም ሾሙላቸው፤ ከጾሙና ከጸለዩም በኋላ ላመኑበት ጌታ አደራ ሰጡአቸው"* (የሐዋ. 14፥23)።

> *"... ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት፥ ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው"* (የሐዋ. 15፥4)።

በዘመናችን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት፥ "ሽማግሌ" መሆን የሚችሉ ሰዎች፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ሆነ በዕለታዊ ኑሯቸው ምን ዓይነት አቋም ያላቸው መሆን እንዳለባቸው የሚገልጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሳይመለከቱ፥ በዓለም ያላቸውን ትምህርት፥ የሥራ ደረጃ እያዩ ብቻ የሚሾሙ እንዳሉ

የታወቀ ነው። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የምናያቸው ሽማግሌዎች የተመረጡት እንደ እግዚአብሔር ቃል ስላልሆነ፥ ፍሬያቸው የሚያጠግብ አይደለም። በዚህ ዓይነት የሽማግሌዎች መንፈሳዊ ሕይወትና መንፈሳዊ ልምምድ ሳይታይ በተመረጡ ሽማግሌዎች፥ ቤተ ክርስቲያን መመራት አለባት ማለት ትልቅ ስህተት ነው። እግዚአብሔር በቤቱ ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ የሚፈልጋቸው፥ መንፈሳዊ የሆኑ፥ ከሌላው ጋር በሕብረት ሊሠሩ የሚችሉትን (team work) እንጂ፥ በሹመት መልክ ሽማግሌ ተብለው የተቀመጡትን እንዳልሆነ ግልጽ ነው። "ለኅብረት አገልግሎት" (team work) አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ምሳሌ ነች። *"በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነብያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፥ ጥቁር የተባለው ስምዖን፥ የቀሬናው ሉክዮስ፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስ ባለምዋል የነበረው ምናሔና ሳውል ነበሩ"* ይላል (የሐዋ. 13፥1)። ከላይ እንዳየነው በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ አምስት አገልጋዮች ነበሩ። አምስቱም የተለያየ ስጦታ ነበራቸው (1 ቆሮ. 12፥28)።

*"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ ነቢያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ* (ኤፌ. 4፥11)። አንዳንድ የመለኮት ትምህርት ምሁራን እነዚህ *"ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌላውያን፥ እረኞችና አስተማሪዎች"* የተባሉት ሁሉም "ሽማግሌዎች" ተብለው ይጠሩ ነበር ይላሉ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውና የአገልግሎት መስካቸው ይለያይ እንጂ፥ አገልግሎታቸው "የሕብረት አገልግሎት" (team work) እንደነበረ ግልጽ ነው። አምስቱም፥ አንደኛው በደረጃ ከሌላው ሳይበልጥ፥ በዕኩልነት ጎን ለጎን ተሰልፈው ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉ ነበር።



ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አምስቱም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያስፈልጋሉ። ከአምስቱ ውስጥ ይሄኛው ወይንም ያኛው አያስፈልግም ማለት አንችልም። ለቤተ ክርስቲያን *"ነብይ፥ አስተማሪ፥ ሐዋርያ፥ የወንጌል ሰባኪ"* ካስፈለገ፥ *"እረኛ"* የማያስፈልግበት ምክንያት አይኖርም። በሌላ በኩል ደግሞ "እረኛ" ካለ፥ የተቀሩት አያስፈልጉም የምንልበት ምክንያት የለንም። "እረኛው" የምዕመናኑን መንፈሳዊ ፍላጎት ብቻውን ማርካት አይችልም። "ሁሉን አንድ ሰው ብቻ ይሥራ" የሚለው አሳብ የእግዚአብሔር ፍላጎትና አሠራር አይደለም። አንድ ሕጻን ሙሉ ሰው ሆኖ እንዲያድግ፥ ሁለቱም ወላጆች ያስፈልጉታል። ልክ እንደዚሁ ቤተ ክርስቲያንም እንድታድግ የሁሉም ስጦታና አገልግሎት ያስፈልጋታል።

በአንድ "እረኛ" (መጋቢ) መመራት ጉዳት አለበት ብለው የሚያምኑ፥ "በሽማግሌዎች ቦርድ" መመራትን ይመርጣሉ። በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ "እረኛ" (መጋቢ) እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ ሽማግሌዎችም ያስፈልጋሉ። *"ቤተ ክርስቲያንን በደንብ የሚያስተዳድሩ፥ ይልቁንም የምሥራቹን ቃል በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር ይገባቸዋል"* (1 ጢሞ. 5፥17) ሲል፥ እዚህ ላይ "እረኛው" (መጋቢው) ከሽማግሌዎቹ እንደ አንዱ ሆኖ ማገልገል እንደሚችል እናያለን። ይህንን እውነት በደንብ መመልከት ባለመቻል፥ አንዳንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚመለከት ነጥብ ላይ ለመወያየት ሲሰበሰቡ፥ መጋቢው አብሯቸው እንዳይሰበሰብ፥ ቢሰበሰብም ድምጽ የሌለው ተመልካች እንዲሆን፥ ወይንም ለሚጠይቁት ጥያቄ መልስ እንዲሰጥ ብቻ ያደርጉታል። ይህ ትክክል አይደለም። መጋቢው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሥራ ድርሻው ከሌሎች ሽማግሌዎች ይለይ እንጂ፥ ከሽማግሌዎቹ መካከል እንደ አንዱ መታየትና መቆጠር አለበት።

የሽማግሌዎች አገልግሎትና ኃላፊነት ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ሽማግሌ" ሲል በዕድሜ ትልቅ የሆነ ማለት እንዳልሆነ እናውቃለን። በዕድሜ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"ማንም ታናሽነትህን አይናቀው"* (1 ጢሞ. 4፥12) ባላለው ነበር። የሽማግሌዎች አገልግሎት ምዕመናኑን ማስተዳደር ነው። *"ቤተ ክርስቲያንን በደንብ የሚያስተዳድሩ፥ ይልቁንም የምሥራቹን ቃል በመስበክና በማስተማር የሚደከሙ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር ይገባቸዋል"* (1 ጢሞ. 5፥17)። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ባደረገው የመሰነባበቻ ንግግር፥ "መንፈስ ቅዱስ እናንተን የመንጋው ጠባቂ አድርጎ ሾሞአችኋልI እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁI ጌታ በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ" አላቸው (የሐዋ. 20፥28)። የሽማግሌዎችን አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው አሳብ ቢሆንም፥ በአግባቡ ካልተጠቀ ምንበት፥ ቤተ ክርስቲያንን በማሳደግ ፈንታ ወደ ኋላ ሊጎትት ይችላል። "እረኛ" (መጋቢ) ሲኖር "የአንድ ሰው የአገዛዝ ሥርዓት" *(Autocracy)* ይሆናል ብለን እንደምንፈራው ሁሉ፥ ሽማግሌዎችም ኃይሉንና ሥልጣኑን እነርሱ ብቻ የያዙት እንደሆነ፥ የጥቂቶች የአገዛዝ ሥርዓት *(Oligarchy)* ሊሆን ይችላል። "አንድ ሰው አይመራንም" በማለት ከመጋቢው እንሸሽ እንጂ፥ በሌላ በኩል "የሽማግሌዎች ሊቀ መንበር" ሙሉ ሥልጣን የያዘ ሌላ "አምባ-ገነን" መሪ ሊሆን እንደሚችል የዘነጋነው ይመስላል። የሽማግሌዎች አመራር የራሱ የሆነ ችግር ሊኖረው ይችላል። ይኸውም፥

4.1. አንዳንድ ሽማግሌዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለማይ መረጡ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግር ይፈጠራል። ትክክል ያልሆነ የአመራር ስልት የሚከተሉ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሙሉ በሙሉ በሕይወታቸው ሳይለወጡ በሽምግልና የሚመረጡ አሉ። የተለወጡ ቢሆኑም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ያላደጉ ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ "አዲስ ክርስቲያን የሆኑትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ እንዳና ደርግ" ቢያስጠነቅቀንም፥ በዓለም ውስጥ ያላቸውን ሥልጣን፥ የነበራቸውን የሥራ ልምምድ፥ በትምህርታቸው ያገኙትን የምሥክር ወረቀት በማየት ብቻ ሥልጣን ላይ እናስቀምጣቸዋለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የማይታይባቸው፥ መንፈሳዊውን ነገር ከዓለማዊ ነገር ጋር የሚቀላቅሉ፥ ሥራው መሠራቱን እንጂ፥ ለነፍሳት ግድ የሌላቸው ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በእንደነዚህ ዓይነት ሽማ ግሌዎች ስትመራ፥ ምን ዓይነት ዕድገትና መሻሻል እንደ ሚኖራት መገንዘብ አያቅተንም። በማሳደግ ፈንታ ወደ ኋላ ይጎትታታል። ስለዚህ ማንኛውም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ሽማግሌዎቻቸውን ሲመርጡ፥ መመሪያቸውን የእግዚአብሔር ቃል ማድረግ አለባቸው።



4.2. እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልተመረጡ ሽማግሌዎች ሌላ ዓይነት የአመራር ሥልት የሚከተሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከውጪ ሲታዩ በጣም መንፈሳዊ የሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ቤት ቅናት ያላቸው ይመስላሉ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እላይ ታች በማለት ብዙ ሲደክሙ ይታያሉ። ይሁን እንጂ፥ ሁሉን ነገር መንፈሳዊ ለማድረግ የሚሞክሩ ናቸው። በጆሮአቸው እግዚአብሔር ካልነገራቸው ምንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ አይፈልጉም። ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያኒቱ በቂ ገንዘብ ባንክ እያላት፥ "የሙዚቃ መሣሪያ ይግዛ" የሚል ሀሳብ ቢቀርብ፥ "ጌታ ምን ይላል?" ብለው የሚጠይቁ ናቸው። እግዚአብሔር በሰጣቸው አዕምሮ መጠቀም "ኃጢአት ነው" ብለው የሚያስቡ ይመስላሉ። ሁሉ ነገር ፍጹም ይሁን ብለው ወግ ሲያጠብቁ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዳታድግ እንቅፋት ይሆናሉ።

## 5. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ "እረኛ" ምን ይላል?

ከአምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች መካከል በዘመናችን ጎልቶ የሚታየው "የመጋቢው" አገልግሎት ነው። "ፓስተር" *(Pastor)* የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው "ፓስቶራሊስ" *(pastoralis)*ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም "እረኛ" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ እንደሆነ ይታያል። *"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝ የለም፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል..."* (መዝ. 23፥1-2)። "እግዚአብሔር ...እንደ እረኛ ለመንጋው እንክብካቤ ያደርጋል፤ ግልገሎቹን በአንድነት ይሰበስባል፤ በእጆቹም አቅፎ ይወስዳቸዋል..." (ኢሳ. 40፥11)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ኢየሱስ ራሱን "መልካም እረኛ" ብሎ ሲጠራ እናያለን። *"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል"* (የዮሐ. 10፥11)። *"በዘላለማዊ ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው የሰላም አምላክ"* (ዕብ. 13፥20)። *"...እናንተ እንደ ጠፉ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል"* (1ኛ ጴጥ. 2፥25)። *"ይህን ብታደርጉ ዋናው እረኛ በሚገለጥበት ጊዜ የማይበላሸውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ"* (1ኛ፥ ጴጥ. 5፥4)።

"መጋቢ-አስተማሪ" ሲባል ሁለት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የያዘ መሆኑን ማወቁ ይጠቅማል። "የመጋቢነት ስጦታ" ለሌሎች የመጠንቀቅ ችሎታ ነው። የበግ እረኛ ለበጎቹ እንደሚጠነቀቀው፥ መጋቢም ለምዕመኑ ይጠነቀቃል። ሁለተኛው ስጦታ፥ ማለትም "ማስተማር" እረኛው ለበጎቹ የሚያደርገውን እንክብካቤ ይገልጻል። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ



"መንፈሳዊ እረኞች" እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በእረኞች ላይ ትንቢት እንዲናገር ሕዝቅኤል አንድ ጊዜ ተልኮ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናያለን። *"የሰው ልጅ ሆይ! የእስራኤልን ጠባቂዎች በመቃወም ትንቢት ተናገርባቸው፤ እኔ ልዑል እግዚአብሔር ስለ እነርሱ የምለውን ሁሉ በትንቢት እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ መንጋውን መንከባከብና መጠበቅ ትታችሁ ራሳችሁን የምትጠብቁ እናንተ የእስራኤል እረኞች ወዮላችሁ!"* (ሕዝ. 34፥2)። በዚህ ትንቢት ውስጥ "እረኛ" ለሚመራው ሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሆነ ይዘረዝራል።

እረኛው በጎቹን መመገብ፥ መንከባከብ፥ መጠበቅ፥ የተሰበሩትን መጠገን፥ የባዘኑትን መመለስ፥ የጠፉትን መፈለግ፥ በዕረፍት ጊዜ የሚያርፉበትን ስፍራ ማመቻቸት ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ የእረኛውን አገልግሎት የበለጠ በዝርዝር ያስረዳል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስን *"ዋናው እረኛ"* (1ኛ ጴጥ. 5፥4) ብሎ ይጠራዋል። የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈውም ሰው ኢየሱስን *"ታላቁ እረኛ"* (ዕብ. 13፥20) ብሎ ሲጠራው፥ ኢየሱስም ራሱን *"መልካም እረኛ"* ብሎ ይጠራ እንደነበር እናውቃለን (የዮሐ. 10፥11)። እርሱ ስለበጎቹ ግድ ይለዋል (የዮሐ. 10፥13)። በጎቹንም በስማቸው ያውቃቸዋል (የዮሐ. 10፥14)። ኢየሱስ ጴጥሮስን ለአገልግሎት ሲጠራው የተጠቀመው "እረኛ" የሚለውን ቃል ነው (የዮሐ. 21፥16)።

እረኛው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወት እንጂ፥ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ወሳኝ "እረኛው" ብቻ አይደለም። አንዳንድ "መጋቢዎች" የቤተ ክርስቲያን እረኛ፥ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ዋና ቁልፍ ነው የሚለውን አሳብ መቀበል ያቅታቸዋል። ይህን የሚሉበት ምክንያት አንዳንዶቹ "ትሁት" በመሆን ሲሆን፥ ሌሎቹ ደግሞ ኃላፊነቱን በመፍራት ለመሸሽ

የሚሰጡት ምክንያት ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እረኛ የሚሆን ሰው፥ ለቤተ ክርስቲያኑ ማደግም ሆነ አለማደግ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል የሚሉ ብዙ ናቸው። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ከተቀጠረ፥ መጋቢው በቤተ ክርስ ቲያኒቱ ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ መሥራት አለበት የሚሉ አሉ። ጥሩ መጋቢ ነው ብለው የሚሉት፥ የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ ሁሉ እርሱ እየሠራ ምዕመናኑን የሚያሳርፍ፥ ከኃላፊነት ነጻ እንዲሆኑ የሚያደርግ ከሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የክር ስቶስ አካል ብዙ የአካል ክፍሎች እንዳሉት አካል ስለሆነ፥ ምዕመናኑ ሁሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያዛል። አካሉ ሕይወት የሚኖረው የአካሉ ክፍሎች ሁሉ በአንድነት አገልግሎታቸውን የሰጡ እንደሆነ ብቻ ነው። ጥሩ መጋቢ ምዕመናኑ ምንም ዓይነት ኃላፊነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ሳይሆን፥ ሁሉም ኃላፊነት ተሰምቷቸው የአገልግሎት ድርሻቸውን እንዲፈጽሙ የሚያደርግ ነው። “መጋቢ” ከብዙ የአካል ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ከመሪዎች መካከል አንዱ ነው። “ዋናው” ወይንም “ራስ” ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መጋቢው ምናልባት መልዕክት ከአንጎል እየተቀበለ፥ ወደሌሎች የአካል ክፍሎች የሚያስተላልፍ “ነርቭስ ሲስተም” ብቻ ሊሆን ይችላል።

☆ ☆ ☆ ☆

# ክፍል ሦስት

## በአገልግሎት የሚገለጡ ስጦታዎች

ምዕራፍ ገጽ

13. ሌሎችን የማገልገል ስጦታ........................ 233

14. የመለገስ ስጦታ........................................ 252

15. የአስተዳደር ስጦታ ................................ 266

16. የምህረት ስጦታ........................................ 284

ምዕራፍ 14

# ሌሎችን የማገልገል ስጦታ

*"...ስጦታችን ሌሎችን ማገልገል ከሆነ፥ በትጋት እናገልግል" (ሮሜ 12፥7)።*

## 1. "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ ምንድነው?

ይህን ስጦታ የግሪኩ ቋንቋ *"አገልግሎት" (Service)* ይለዋል። "አገልግሎት" የሚለው ቃል በዘመናችን የማንኛውም *መንፈሳዊ ሥራ መግለጫ* ስለሆነ፥ *"ከማገልገል ስጦታ" ጋር* አንድ አድርገን እንዳናየው መጠንቀቅ ያስፈልገናል። በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የተሰለፈውን ሰው *"አገልጋይ"* ብለን እንጠራዋለን። ይሁን እንጂ፥ *"ሌሎችን የማገልገል" (Service)* ስጦታ አለው ማለት አይደለም። *"ዲያቆን"* የሚለው ቃል የመጣው *"ዲያኮኖስ* ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ቀጥ ተኛ ትርጉሙ *"አገልጋይ ወይንም አሽከር"* ማለት ነው።



ይህም ማለት፥ ኢየሱስ አማኞችን ለአገልግሎት ሲጠራን፥ ባሪያ፥ ወይም አሽከር እንድንሆን እንጂ፥ "ጌቶች" ሆነን በምናገለግላቸው ሰዎች ላይ እንድንሰለጥን አይደለም። ኢየሱስ ሌሎችን ለማገልገል ነፍሱን እንደ ሰጠ፥ እኛም ለአገልግሎት ሕይወታችን የተሰጠ መሆን አለበት። ነገር ግን ሁላችንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት ተሳትፎ ይኑረን እንጂ፥ አማኞች ሁሉ *"ሌሎችን የማገልገል"* ስጦታ አለን ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።

ኢየሱስ ሌሎችን እንደሚገባ ማገልገል እንድንችል ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ፥ ብዙዎቻችን ስጦታችን ምን እንደሆነ ለይተን ስለማናውቅ፥ በስጦታችን አንጠቀምም። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንደኛው፥ *"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ"* ነው። *"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ"* ምንድነው? *ፒተር ዋግነር፥* "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ምን እንደሆነ ሲገልጹ፥ *"እግዚአብሔር ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባሎች፥ የሌሎችን ችግር ተረድተው፥ ባላቸው ነገር ሁሉ ተጠቅመው፥ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ለመርዳት የሚያስችላቸውን የተለየ ኀይል፥ አቅምና ችሎታ ሲሰጣቸው ነው"* ይላሉ። የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) ጤናማ ሆና እንድትታነጽና እንድታድግ፥ *"ሌሎችን የማገልገል"* ስጦታም ያስፈልጋታል። ይህ ስጦታ፥ እንደ አንዳንዶቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፥ ስጦታው ያለውን ሰው፥ በሰው ፊት ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርግ ስጦታ አይደለም። በዚህ ምክንያት ስጦታው በአንዳንድ አማኞች ዓይን አነስተኛ ሆኖ መታየቱ አይቀርም። ይሁን እንጂ፥ በቤተ ክርስ ቲያን ውስጥ የማያስፈልግ፥ ወይንም በሁለተኛ ደረጃ ሊታይ የሚገባ ስጦታ አይደለም። ጳውሎስ ጎልተው የማይታዩትን "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን" አቃለው እንዳያዩ ለቆሮንቶስ

አማኞች ምክር ሲሰጥ፥ *"ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው፤ ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፤ በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል"* አላቸው (1ኛ ቆሮ. 12፥22-23)።

የሥነ መለኮት ሊቃውንት "መንፈሳዊ ስጦታ" ምን እንደ ሆነ የተለያየ መግለጫ ሲሰጡ እናያለን። ሃዋርያው ጴጥሮስ ግን በቀላሉ ልንረዳውና ልንይዘው በምንችለው መንገድ ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል። *"እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል"* ይላል (1 ጴጥ. 4፥10-11)። "መንፈሳዊ ስጦታ" ማለት ሌሎችን የምናገለግልበት ግልጽ የሆነ የጸጋ ስጦታ ነው። በመንፈሳዊ ስጦታችን ሌሎችን ስናገለግል፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሌሎች መግለጻችን ነው። እኔና እናንተ ሌሎችን ማገልገል የምንችለው በራሳችን ኃይል፥ ወይም ጉልበት ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ ስጦታ ማለት ግልጽ በሆነ መንገድ ሌሎችን እንድናገለግል የሚያስችለን ኃይል ነው።

ምዕመናን ሁሉ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት ድርሻ እንዲኖራቸው መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዳቸው "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን" እንዳከፋፈላቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቢናገርም፥ በዘመናችን "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን" አውቀው አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት ግን በጣም የተወሰኑ አማኞች ናቸው። የክርስቶስ አካል ማደግና ብዙ ፍሬ ማፍራት የምትችለው፥ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ስጦታውን አውቆ በአግባቡ መጠቀም የቻለ እንደሆነ ነው። በዘመናችን ያለችው



ቤተ ክርስቲያን ፍሬዋ የበዛ፥ ዕድገትዋ የተፋጠነ እንዳይሆን እንቅፋት ከሆኑባት ምክንያቶች መካከል አንደኛው፥ በጣም የተወሰኑ ክርስቲያኖች ብቻ አገልግሎታቸውን ስለሚፈጽሙ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት፥ ጥቂቶች ብቻ ሳይሆኑ፥ አማኞች ሁሉ የአገልግሎት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ነው። ሁሉም የአገልግሎት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ስንል ግን፥ አማኞች ሁሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ይሆናሉ ማለት እንዳልሆነ ልንረዳ ይገባል።

ጳውሎስ *"እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዲኖረው አድርጓል"* (1 ቆሮ. 12፥28) ይልና፥ ስጦታዎችን ተራ በተራ ይዘረዝራል። ከዘረዘራቸው ስጦታዎች መካከል፥ *"...ሰዎችን የማገልገል ስጦታ"* አንደኛው ነው። በሰው ዘንድ ጎልተው እንዲታዩ በሚያደርጋቸው አንዳንድ አገልግሎቶች ውስጥ ገብተው ለመሳተፍ ብዙ ክርስቲያኖች ፍላጎት አላቸው። ሥጦታው ባይኖራቸውም፥ መስበክ፣ ማስተማር፣ ስብሰባ መምራት፣ መዘመር ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ፥ ሁሉም ሰባኪና አስተማሪ መሆን ስለማይችል፥ ከላይ የጠቀስናቸውን አገልግሎቶች ለመያዝ በሚፈልጉት ምዕመናን ልብ ቅሬታ ይፈጠራል። ቁጥራቸው ይህን ያህል ብዙም ባይሆንም፥ የመድረክ አገልግሎት የማያምራቸው፥ ወይንም በሰው ዘንድ መታየት ፈጽሞ የማያጓጓቸው አንዳንድ አማኞች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ፥ ዕርዳታ የሚያስፈልገው አንድ ሰው አጋጥሟቸው፥ ያንን ሰው መርዳት ከቻሉ፥ ልዩ የሆነ ደስታ የሚሰማቸው ከመሆናቸውም በላይ፥ ይህ አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ በመጨረሻው ቀን ሽልማት እንደሚያሰጣቸው የሚያውቁና የሚያምኑ ናቸው። ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ፈልገው መጓጓዣ ላጡ ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት፥ በሥጋ ደካማ የሆኑትን የቤተ ክርስቲያን አባሎችም ሆነ ሌሎችን እቤታቸው ድረስ ሄደው የቆሸሸውን ቤታቸውን

በመጥረግ፣ ምግብ በመቀቀል፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ አገልግሎት በመስጠት ልዩ ደስታ የሚሰማቸው ናቸው።

"መስበክ፣ ማስተማር፣ መዘመር አልችልም፤ ሌሎችን ማገልገል፥ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዕርዳታ መስጠት ግን እችላለሁ። የማገለግለውም ሸክም ሆኖብኝ፥ ወይንም ተጨንቄ ሳይሆን፥ ደስ እያለኝ ነው" የሚሉ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጥረጊያ ይዘው ቆሻሻ የሚጠርጉ፥ ወንበር የሚደረድሩ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎች ችላ ያሉትን ሥራ የሚሠሩ፥ አንዳንድ ምዕመናን አዝረክርከውት የሄዱትን ዕቃ አንስተው በቦታው የሚያስቀምጡ፥ ከሰው ሁሉ በፊት መጥተው የቤተ ክርስቲያን በር የሚከፍቱ፥ ፕሮግራሙ እንዳለቀ ሰው ሁሉ ወደቤቱ ሲሄድ፥ ወደ ኋላ ቀርተው የቤተክርስቲያን በር ዘግተው፥ መጨረሻ ላይ ወደ ቤታቸው የሚሄዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች እንዳሉ እናውቃለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹ አብዛኛዎቹ *"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ"* እንዳላቸው በግልጽ ያስታውቃል።

ስጦታው ባይኖራቸውም፥ ኃላፊነት ተሰምቷቸው ወይንም ግዴታ ስለሆነባቸው ብቻ ከላይ የገለጽናቸውን ዓይነት አገልግሎቶችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡ አንዳንድ አማኞች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የሚያገለግሉት "ከእኔ ይጠበቅብኛል" ብለው በማሰብ፥ ወይንም ይሉኝታ በመፍራት ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው። *"የማገልገል ስጦታ"* ያላቸው ግን የሚያገለግሉት፥ ይሉኝታ ፈርተው፥ ወይንም ግዴታ ሆኖባቸው ሳይሆን፥ ሌሎችን ማገልገል ደስ ስለሚላቸው ብቻ ነው። "ሌሎችን ማገልገል፥ መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝ ስጦታዬ ነው" ብለው ስለሚያምኑ፥ የሚያገለግሉት እያጉረመረሙ፥ ወይንም እየተነጫነጩ ሳይሆን፥ ደስ ብሏቸው ነው። እነዚህ፥ "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" እንዳላቸው ግልጽ ነው።



## 2. "ሌሎችን የመርዳት" አገልግሎት፥ ጎልቶ የሚታይ አገልግሎት አይደለም

*"ሌሎችን የመርዳት (የማገልገል) ስጦታ"* ያላቸው ሰዎች፥ አገልግሎታቸውን የሚሰጡት በሰው ዘንድ ለመታወቅ፥ ወይንም ለክብር ፍለጋ ስላልሆነ፥ አገልግሎታቸውን ሰዎች ባያዩላቸው፥ በአገልግሎታቸው ምክንያት ታዋቂ ባይሆኑም ፍጹም ግድ የላቸውም። የሚያገለግሉትም ራሳቸውን በማተለቅ ሳይሆን፥ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ስለሆነ፥ በአደባባይ ጎልተው አይታዩም። በእግዚአብሔር ፊት ግን እነርሱም ሆኑ አገልግሎታቸው ስለማይደበቅ፥ ዋጋቸው በሰማይ ታላቅ እንደሚሆን ያውቃሉ።

ጳውሎስ *"ስጦታችን ሌሎችን ማገልገል ከሆነ በትጋት እናገልግል"* (ሮሜ 12፥7) ያለው፥ ስጦታው ቢኖረንም ያለ ትጋት ማገልገል እንደሚቻል ሲገልጽ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎቻችን ሊዳብሩ የሚችሉት፥ በተግባር ላይ ያዋልናቸው እንደሆነ ብቻ ነው። "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" *ማለት፥ ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ዓይነት ድጋፍ፥ ገንዘብም ሆነ ሌላ ቁሳቁሳዊ ነገር በደስታ ለመስጠት የሚያስችል ስጦታ ማለት ነው።* ስጦታው ያላቸው ሰዎች በትጋት እንዲያገለግሉ የሚያደርጋቸው ትልቁ ምክንያት የሌሎችን ችግር፥ የሌሎችን ሸክም ማቃለል ደስ ስለሚላቸው ብቻ ነው።

*"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ"* ብዙ ጊዜ በአደባባይ ወይንም በሰው ፊት የሚታይ ባይሆንም፥ ከእግዚአብሔር ዓይን ግን የተሰወረ አይደለም። በመጨረሻው ቀን፥ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሲቆሙ፥ ብዙ አማኞች በዚህ አገልግሎታቸው ምክንያት ሽልማታቸውን የሚቀበሉ መሆናቸውን እናውቃለን። ጳውሎስ *"ሄኔሲፎሩን"* ስለ ሰጠው አገልግሎቱ እንዲሆንለት የተመኘውን ሲገልጽ *"በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው"* (2 ጢሞ. 1፥18) ይላል። ዕርዳታ የሚያስፈል

ጋቸውን መርዳት፣ ማነቃቃት እንደማንኛውም አገልግሎት በመጨረሻው ቀን በጌታ ፊት ሽልማት ያስጣል። መንፈስ ቅዱስ ሥጦታን ለአማኞች የሚያከፋፍለው፣ ስጦታው የተሰጣቸው አማኞች ይዘውት እንዲቀመጡ፣ ወይንም ራሳቸውን እንዲጠቅሙበት ሳይሆን፣ ሌሎችን እንዲያገለግሉበት ብቻ ነው። ስለሆነም፣ ታማኞች ሆነው በስጦታቸው የማይጠቀሙበት፣ በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርቡ ይጠየቁበታል (የማቴ. 25፥19-30)። እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ የሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ *"ሌሎችን የማገልገል ሥጦታ"* ከሆነ፣ "ለምን አልሰበክም? ወይንም ለምን አላስተማርክም?" ብሎ በኃላፊነት አይጠይቀንም። ነገር ግን ዕርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ሲያጋጥመን፣ ለዚያ ሰው የጎደለውን እንድናሟላ እግዚአብሔር ወደ እኛ ሲልከው፣ አስፈላጊውን ዕርዳታ ካላደረግን ግን፣ ተጠያቂ ነን።

እዚህ ላይ አንድ ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር፣ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች መርዳት፣ ሥጦታው ያላቸው አማኞች ኃላፊነት ነው ብለን ችላ ብንል፣ በመጨረሻ ቀን ሁላችንም ተጠያቂዎች እንደምንሆን ነው። *"በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፥ እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ፥ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና። እነርሱ ደግሞ ይመልሱና ጌታ ሆይ! ተርበህ ወይስ ተጠምተህ፥ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ፥ ወይስ ታመህ፥ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል። ያን ጊዜ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት፥ ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል። እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ"* ይላል (የማቴ. 25፥41-46)። የዘመኑ ክርስቲያኖች "ሌሎችን ማገልገል"



የሚለውን አሳብ ፈጽሞ ችላ ያልነው ይመስላል። ምክንያታችን ምን ይሆን? "የዳንነው በጸጋ እንጂ፥ በበጎ ሥራ አይደለም" በማለት በጎ ሥራን ችላ በማለታችን ነው። ስለሆነም አብረውን ላሉትም ሆነ ከእኛ ውጪ ላሉት ችግራቸውን በግልጽ ብናይም፣ በጎነት ለማሳየት ምንም ዓይነት እርምጃ አንወስድም። የታወቀው *ጆን ዌስሊ፥ "በተቻላችሁ መጠን፥ በአላችሁ አቅም፥ በምትችሉት መንገድ ሁሉ፥ በማንኛውም ሥፍራ፥ በማንኛውም ጊዜ፥ ለማንኛውም ሰው፥ ማድረግ የምትችሉትን በጎ ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አትበሉ"* በማለት ያስተምር ነበር። ማስተማር ብቻ ሳይሆን፣ ያስተማረውን በተግባርም ይገልጸው እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል።

## 3. "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ ካላቸው መካከል፥ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ

*"ሌሎችን መርዳት"* ወይንም ማገልገል ጥቂቶች ብቻ የሚሳተፉበት አገልግሎት ሳይሆን፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያደርጉት የሚገባ መንፈሳዊ ተግባር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጳውሎስ ክርስቲያኖች ያለባቸውን ኃላፊነት ሲገልጽ *"የክርስቶስ አካል የሆንችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምዕመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው"* ይላል (ኤፌ. 4፥12)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሌሎችን የማገልገል ልብ ወይንም ስጦታ የነበራቸው ብዙዎች እንደነበሩ እናውቃለን። ከእነርሱም መካከል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

### 3.1. ሄኔሲፎሩ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ሌሎችን የመርዳት ወይንም የማገልገል ስጦታ" ካላቸው አማኞች መካከል ጎልቶ የሚታየው፥ ጳውሎስ በጣም ያደነቀውና የወደደው፥ ሄኔሲፎሩ የተባለው አማኝ ነው። ጳውሎስ ይህ ሰው ምን እንዳደረገለት ለጢሞቴ

ምስ ሲገልጽለት፥ *"ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን ይስጥ፤ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፤ በሰንሰለቴም አላፈረበትም፤ ነገር ግን በሮሜ ባደረ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ፤ በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤ በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደኅና ታውቃለህ"* አለ (2 ጢሞ. 1፥16-18)።

ጳውሎስ *"ሄኔሲፎሩን"* ያመሰገነበት፥ ወይንም ያደነቀበት ምክንያት ለመሆኑ ምን ይሆን? በአዕምሮው የላቀ ሰው በመሆኑ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ስለነበረው፥ እንዲሁም የልዩ ልዩ ኮሚቴዎች አባል በመሆኑ፥ ወይንም የልዩ ልዩ አገልግሎቶች ሊቀ መንበር በመሆኑ ሳይሆን፥ ጳውሎስ ወህኒ ቤት በታሠረበት ጊዜ መጥቶ ስለ ጎበኘው ብቻ ነው። እንደ ወንጀለኛ ይታይ ከነበረው ጳውሎስ ጋር መታየት ችግር የሚያስከትል ቢሆንም፥ ከጳውሎስ ጋር መታየቱ አላሳፈረውም። ጳውሎስን በመፈለግ እላይ ታች በማለት ብዙ ደክሟል። ይህን ያዩ አንዳንድ አማኞች ሄኔሲፎሩን "ሥራ ፈት፥ ለቤተ ሰቡ የማያስብ ሰው" እንደሆነ አድርገው እንደሚገምቱት ግልጽ ነው። ቢሆንም፥ እነርሱ ለሚሰጡት አስተያየት ይህን ያህል ግድ አልነበረውም። ወህኒ ቤት በተደጋጋሚ በመምጣቱ ምክንያት አንዳንድ የወህኒ ቤት ዘበኞች "ዓላማው ምንድነው?" ብለው ሳይ ጠራጠሩት እንዳልቀሩ እንገምታለን። ይሁን እንጂ፥ በልቡ ውስጥ ምንም ዓይነት ፍርሃት አልነበረም። "የማገልገል ሥጦታውን" በተግባር ላይ ለማዋል በመሞከሩ፥ ጎረቤቶቹ "ሥራ ፈት ነው" እያሉ ቢያስወሩበትና እንዲሁም ብዙ ዋጋ ቢያስከፍለውም፥ ከአገልግሎቱ ትንሽም ቢሆን ወደ ኋላ አላለም።

*"ሄኔሲፎሩ"* አገልግሎቱን ለመፈጸም ምን ያህል ትጋት እንዳሳየ ስንመለከት፥ ጳውሎስ ስለ እርሱ የሰጠው አስተያየትና አድናቆት ከመሥመር የወጣ እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ለአገልግ



ሎቱ ሙሉ ልብ የሰጠው ባይሆን ኖሮ፥ ጥቂት ከሞከረ በኋላ "ጳውሎስን ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም" በማለት አርፎ መቀመጥ ይችል ነበር። ሮም ውስጥ ብዙ ወህኒ ቤቶችን ያጣበቡ ብዙ እሥረኞች ስለነበሩ፥ አንድ እሥረኛ ፈልጎ ማግኘት ቀላል አልነበረም። *"ሄኔሲፎሩ"* ከአንዱ ወህኒ ቤት ወደ ሌላው ወህኒ ቤት እየዞረ፥ ተስፋ ሳይቆርጥ ጳውሎስን ይፈልግ ነበር። ለዚህ ነው ጳውሎስ *"ፈልጎ፥ ፈልጎ አገኘኝ"* ያለው። ጳውሎስን ደስ የሚለው የአማኞችን ይዞታ፥ በእምነታቸው ማደግና መጽናታቸውን መስማት እንደሆነ ስለሚያውቅ ጥሩ ጥሩ ዜና ይዞለት እንደሄደ እንገምታለን። እንዲሁም ወህኒ ቤት ውስጥ በቂ ምግብ ስለሌለ፥ የአገልግል ምግብ ብዙ ጊዜ ይዞለት እንደሄደ እናምናለን። ጳውሎስ *"ሄኔሲፎሩ"* ያደረገለትን ሲገጽል፥ *"ብዙ ጊዜ አሳርፎኛል"* ይላል።

በዘመናችንም "ሌሎችን በማገልገል ሥጦታ" ጌታ የባረካችሁ አማኞች እንዳላችሁ አምናለሁ። የታመመን መጎብኘታችሁ፥ የተረሳውን መፈለጋችሁ፥ የታሠረውን መጠየቃችሁ፥ "ስለ እኔ ማንም ግድ የለውም" በማለት ስለ ራሳቸው ዝቅተኛ ስሜት የሚሰማቸውን፥ "እግዚአብሔር እኔን አይወደኝም" በማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚጠራጠሩትን፥ በማያስቡትና በማይጠብቁት ሁኔታ ስትጎበኙአቸው፥ ስትደርሱላቸውና ስታገለግሏቸው፥ አንዳንዶች ሥራ ፈት አድርገው ቢያዩአችሁም፥ በምትረዷቸው ሰዎች ሕይወት ግን ከፍተኛ ለውጥ እንደምታመጡ እወቁ። ብዙ ሰዎች፥ የልባቸውን አሳብ የሚያጫውቱት፥ ጆሮውንና ልቡን ከፍቶ የሚያዳምጣቸው ሰው ይፈልጋሉ። ብዙ ነገር ማድረግ ባንችል እንኳን፥ የሌላውን ጭንቀት ቁጭ ብለን ብናዳምጥ ከፍተኛ "አገልግሎት" መፈጸማችንን እንደሆነ እንወቅ።

*"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ"* ያላቸው አማኞች፥ የሚያገለግሏቸውን ሰዎች አይመርጡም። ለደጎች ብቻ ሳይሆን

ለክፉዎችም፥ ለወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ለጠላቶቻቸውም መልካም ነገርን ያደርጋሉ። ተገፍተው፥ ሳይወዱ በግድ የሚያደርጉት ነገር ሳይሆን፥ ደስ ብሏቸው የሚያደርጉት ነው። ሌሎችን የማገልገል ስጦታ ከነበራቸው የጥንት መንፈሳዊ አባቶች መካከል ጎልቶ የሚታየው *"የአሲሱ ፍራንሲስ"* (Francis of Assis) ነው። አንድ ጸሐፊ ፍራንሲስን ሲገልጸው፥ *"በታላቅ መከራ፥ በጉስቁልና፥ በጭንቀትና በማጣት ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ሲያጋጥሙት፥ ከእነርሱ በመሸሽ ፈንታ፥ ስብራታቸውን ለመጠገን፥ ቁስላቸውን ለመፈወስ ልቡ ወሰን በሌለው ርህራሄ ተሞልቶ ፊቱን ወደ እነርሱ ያዘነብላል። የፍቅርን ጥሬ ቃል ብቻ ለሌሎች በመስበክ ፈንታ፥ ፍቅርን በተግባር አውሎ ያስተምራል። መድኃኒትና ሕክምና ወደማያስፈልጋቸው በመሄድ ፈንታ ወደታመሙት፥ ወደተረሱትና ፈላጊ ወደሌላቸው ፊቱን ያዞራል። ለድሆች፥ ማንም ለማይፈልጋቸው፥ ፍጹም ለጠፉት፥ ለለምጻሞችና ለወንበዴዎች ራሱን አሳልፎ ይሰጣል"* አለ።

## 3.2. ዶርቃ

በአዲስ ኪዳን "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ ካላቸው አማኞች መካከል አንደኛዋ *"ዶርቃ"* ነበረች። ስለ እርሷም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። *"በኢዮጴም ጣቢታ የምትባል አንዲት አማኝ ነበረች። የስሟም ትርጉም በግሪክኛ ዶርቃ ወይም ሚዳቋ ማለት ነው፤ እርስዋ መልካም ነገር ማድረግና ለድሆች መለገስ የምታዘወትር ሴት ነበረች"* (የሐዋ. 9፥36)። ዶርቃ "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ ስለነበራት ልብስ ለሌላቸው መበለቶች ቀሚሶችንና ልብሶችን እየሰፋች ታለብስ ነበር። ዶርቃ አንድ ቀን በጣም ታመመችና ሞተች። በበጎ ተግባሯ ልባቸው የተነካ አንዳንድ መበለቶች ሞቷን አምነው መቀበል አቃታቸው። ጉድጓድ ቆፍረው፥ አፈር አልብሰውና ቀብረዋት መመለስ ስላቃታቸው፥ ጴጥሮስ በቶሎ እንዲመጣ መልዕክተኛ ላኩበት።



ሞቷ ውስጣቸውን ይበላቸውና ያቃጥላቸው ነበር። *"...መበለቶቹ ሁሉ በዙሪያው ቆመው እያለቀሱ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር በሕይወት ሳለች የሠራቻቸውን ቀሚሶችና ልብሶች ያሳዩት ነበር"* (የሐዋ. 9፥39)። በዚህ ዓይነት ዶርቃ ሌሎችን የማገልገል ስጦታ እንደነበራት በግልጽ እናያለን።

## 3.3. በርናባስ

በአዲስ ኪዳን "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ከነበራቸው አማኞች መካከል ሌላው በርናባስ ነበር። ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ አሳልፎ የሰጠ፥ እግዚአብሔር በሕይወቱ ያቀደለት በጎ ነገር እንዲፈጸም ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሰጠ ሰው ነበር። በርናባስ የራሱን ጥቅምና ፍላጎት የተወ ደግ ሰው ነበር። የተረፈውን፥ የማይፈልገውን ሳይሆን፥ አንድም ሳያስቀር ለእግዚአብሔር መንግሥት ማስፋፊያ እንዲሆን ያለውን ሀብትና ንብረት የሰጠ ሰው ነበር። *"እርሻም ነበረውና ሸጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው"* ይላል (የሐዋ. 4፥37)። ብዙዎቻችን የምንሰጠው ከራሳችን አጉድለን ሳይሆን፥ የተረፈንን፥ ፍርፋሪያችንን፥ ጨርሶ የማንጠቀምበትን ነው። በርናባስ "ሌሎችን በማገልገል" መንፈስ የተሞላ ስለነበረ፥ ዓይኖቹ የተጎዱትን፣ የቆሰሉትን፣ ያዘኑትን፣ ተስፋ የቆረጡትን ያዩ ነበር። ጆሮቹ የመከራ ሰዎች የሚጮሁትን ጩኸት የመስማት ችሎታ ነበራቸው። መስማትና ማየት፥ ወይንም ከንፈር መጥጦ ማለፍ ብቻ ሳይሆን፥ የመጽናናት አገልግሎት በመስጠት የታወቀ ሰው ነበር። "በርናባስ" የሚለው ስም፥ የቅጽል ስሙ እንጂ፥ ትክክለኛ ስሙ "ዮሴፍ" ነበር። *"ትውልዱ የቆጵሮስ ሰው የነበረ አንድ ሌዋዊ ዮሴፍ የሚሉት ነበረ፤ እርሱም በሐዋርያት በርናባስ ተባለ፤ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው"* (የሐዋ. 4፥36)።

በዓለማችን “ሌሎችን በማገልገል” ስጦታ ከተሞሉት ታላላቅ ሰዎች መካከል የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት *“አብርሃም ሊንከን”* አንደኛው ሰው ናቸው። ለተጎዱት፣ ላዘኑት፣ ተስፋ ለቆረጡት ሰዎች የሚራራ ልብ ነበራቸው። በአሜሪካ ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት *(Civil War)* በነበረበት ወቅት፥ በጦርነቱ ምክንያት የቆሰሉትን በሽተኞች ሁልጊዜ ማታ ማታ ይጎበኙ ነበር። አንድ ጊዜ በጦርነቱ ውስጥ ተመትቶ ሁለት እግሩ የተቀረጠውን ወጣት ጠጋ ብለው ካነጋገሩት በኋላ “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?” ብለው ጠየቁት። ያም ወጣት ማንነታቸውን ሳላወቀ፥ “ከጠየቅኸኝ አጠገቤ ቁጭ በልና ለእናቴ ደብዳቤ ጻፍልኝ” አላቸው። አብርሃም ሊንከንም ቁጭ ብለው ልጁ ጻፍ የሚላቸውን መጻፍ ጀመሩ። በጦርነቱ በጣም እንደተጎዳና እንደ ቆሰለ፥ ሀኪሞችም የመዳን ተስፋ እንደሌለው እንደ ነገሩት ገልጾ ጻፈ። ደብዳቤውን ጽፈው ሲጨርሱ መጨረሻ ላይ፥ ጸሐፌው፥ አብርሃም ሊንከን ብለው አስፈሩ። ያ ወጣት ደብዳቤውን የጻፉለትን ሰው ስም ሲያይ ተደንቆ “አንተ አብርሃም ሊንከን፥ ፕሬዚደንታችን ነህ እንዴ?” ብሎ ጠየቃቸው። “አዎን” የሚል መልስ ከሰጡት በኋላ “ፕሬዚዳንት መሆኔን ካወቅህስ በኋላ ምን እንዳደርግልህ ትጠይቀኛለህ?” አሉት። ያም ወጣት፥ “አጠገቤ ቁጭ ብለህ እጄን ያዘኝI በሞት ሸለቆ ውስጥም ሳልፍ እየኝ” አላቸው። አብርሃም ሊንከንም ያ ወጣት እስኪሞት ድረስ እጁን ይዘው አጠገቡ ለረጅም ጊዜ ተቀመጡ። እውነተኛ “አገልግሎት” ይህንን ይመስላል። “ሌሎችን የማገልገል” ስጦታ ያላቸው አማኞች፥ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች የሚያዩት እግዚአብሔር በሚያይበት ዓይን ነው። ለተጎዱት፣ ለቆሰሉት፣ ላዘኑት፣ ተስፋ ለቆረጡት እግዚአብሔር የሚራራ ልብ ሰጥቷቸዋል።



## 4. “ሌሎችን የማገልገል ስጦታ” ያላቸው መለያቸው (Characteristic) ምንድነው?

በሮሜ 12፥6-8 ከተዘረዘሩት የጸጋ ስጦታዎች ውስጥ “ሌሎችን ማገልገል” የሚለው ስጦታ ሁለተኛው ነው። ጳውሎስ ሁሉም በተሰጠው ስጦታ እንዲተጋ ያሳስባል። *“...አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ...”* ይላል። “የማገልገል ስጦታ” ያላቸው አማኞች መለያቸው ምንድነው?

### 4.1. ዕርዳታ ለሚያስፈልገው ሰው ዕርዳታ ለመስጠት፥ ቶሎ ደራሽ ናቸው

“ሌሎችን የማገልገል ስጦታ” ያላቸው አማኞች ዕርዳታ የሚያስፈልገውን ሰውም ሆነ ሁኔታዎችን ቶሎ የማየት ችሎታ አላቸው። ዕርዳታ ማስፈለጉን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ዕርዳታ ለመስጠት፥ ወይንም ለማገልገል ከፍተኛ የሆነ ፍላጎትና መነቃቃትም አላቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህን ዓይነት ስጦታ ያላቸውን አማኞች በቀላሉ መለየት ይቻላል። ወለል ሲጠርጉ፥ ወንበርና ጠረጴዛ ሲደረድሩና ሲያስተካክሉ፥ የቤተ ክርስቲያን በር ሲከፍቱና ሲዘጉ የሚታዩት ሌሎችን የማገልገል ስጦታ ያላቸው ናቸው። በእንግድነት ሰው ቤት ሄደው ከሌሎች እንግዶች ጋር ሳሎን ተቀምጠው መጫወታቸውን ትተው፥ ወጥ ቤት ገብተው የሚረዱ፥ የተበላሸ ነገር ሲያዩ ያንን ለመጠገንና ለማስተካከል የሚታገሉ ይሄ ስጦታ ያላቸው ናቸው። የሚረዳ ነገር ካለ ማንም ሳይጠይቃቸው መርዳት ተፈጥሯቸው ነው። ሁልጊዜ ወንበር የሚደረድሩ፥ አጣጥፈው የሚያስቀምጡ፥ የተበላበትና የተጠማበትን ዕቃ የሚሰበስቡ ይሄ ስጦታ ያላቸው ናቸው። የሚያስደንቀው ማንኛቸውንም ነገር የሚያደርጉት ደስ ብሏቸው እንጂ፥ “ኃላፊነት ወይንም ግዳጅ አለብኝ” ብለው አይደለም። ሁልጊዜ የአገልጋይ ልብ *(servant's heart)* አላቸው።

## 4.2. "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ያላቸው፥ በእጅ የሚሠራ ነገር ደስ ይላቸዋል

ይሄ ስጦታ ያላቸው አብዛኞዎቹ የእጅ ሙያ ያላቸው ናቸው። የተሰበረ ዕቃ ለመጠገን፥ የተበላሸ ነገር ለማስተካከል ልዩ የሆነ ችሎታ አላቸው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት ልዩ ልዩ የአካል ክፍሎች ውስጥ "እጅ" ተብለው የሚጠሩት፥ ይህን ዓይነት ስጦታ ያላቸው አማኞች ናቸው። "የማገልገል ስጦታ" ያላቸው፥ አብዛኞዎቹ በእጅ የሚሠራውን ማንኛውንም ነገር የመሥራት ፍላጎት አላቸው። ካላቸው የእጅ ሙያ በተጨማሪ፥ ያለሥርዓት የተቀመጠ፥ የቆሸሸ ነገር ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ሰው ቤት፥ አይተው ዝም ማለት ወይንም መታገስ ፈጽሞ አይችሉም። ባይጠየቁም፥ ያልተስተካከለውን ማስተካከል፥ የቆሸሸውን ማጠብ ደስ ይላቸዋል። ይህን የሚያደርጉት ምስጋና ፈልገው አይደለም። ሌላው ቀርቶ አንዳንድ ጊዜ የሚያደርጉለት ሰው ቅር እንደሚለው ቢያውቁም እንኳን ያደርጉታል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ችግሮች የሚፈጠሩት፥ አንዳንድ ምዕመናን ስጦታቸው ባልሆነ አገልግሎት ውስጥ በፈቃዳቸው ወይንም ያለፈቃዳቸው ተገፍተው ሲገቡ ነው። የመስበክ ወይንም የማስተማር ስጦታ እንደሌላቸው በግልጽ ቢያውቁም፥ መድረክ ላይ መቆሙ ይፈትናቸውና "ካላስተማርኩ" ወይንም "ካልሰበክሁ" ይላሉ። ዕድሉ ሲሰጣቸው ምዕመናኑ ባዶውን መጥቶ ባዶውን እንዲመለስ ያደርጋሉ። ዕድል ካልተሰጣቸው ደግሞ በመሪዎች ላይ ያኮርፋሉ፤ የከፋ እንደሆነ የተለያየ ምክንያት ፈጥረው አድማ ያስነሳሉ። ምዕመናን ያለስጦታቸው ገብተው ሲያገለግሉ ከማበላሸታቸውም ሌላ እነርሱም ቢሆኑ በአገልግሎታቸው ደስተኞች አይሆኑም።



## 4.3. "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ያላቸው፥ ዕርዳታ ሲጠየቁ "ዕምቢ" ማለት አይችሉም

"ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ያላቸው አማኞች፥ ሁል ጊዜ ሌሎችን ማገልገል ወይንም መርዳት ደስ ስለሚላቸው፥ ቀደም ሲል የተቀበሉት ብዙ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም፥ ዕርዳታቸውን የሚፈልግ ሰው ሲመጣ "እምቢ! አልችልም! ዛሬ ጊዜ የለኝም" ማለት በጣም ይከብዳቸዋል። በዚህ ምክንያት ከአቅማቸው በላይ ራሳቸውን ኃላፊነት ውስጥ ይከታሉ። "ይሄ ነገር የሚሠራው እንዴት ነው?" ተብለው ቢጠየቁ እንኳን፥ "እንዲህ አድርጋችሁ ሥሩት" በማለት ፈንታ፥ "እኔ መጥቼ እሠራዋለሁ" ይላሉ። የተጠየቁትን ሁሉ "እሺ!" ሲሉ፥ "ይሄን ሁሉ እንድሠራ፥ ወይንም እነዚህን ኃላፊነቶች ሁሉ እንድቀበል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይ?" ብለው ፈጽሞ ራሳቸውን አይጠይቁም። ጊዜ በማጣት ለመርዳት የሚፈልጉትን ሰው በጊዜውና በሰዓት መርዳት ባለመቻላቸው ምክንያት፥ ዕርዳታቸውን የሚጠብቀው ሰው፥ ዕርዳታውን ማግኘት ሲያቅተው፥ "መጀመሪያ ለምን እሺ አለኝ? እሺ ካለኝ ለምን ቃሉን አይጠብቅም?" በማለት ይቀየማቸዋል። በየጊዜው ይህንን የመሰለ ችግር ቢያጋጥማቸውም ብዙ ጊዜ ራሳቸውን አያርሙም። ዕርዳታቸውን የሚፈልግ ሰው ሲያጋጥማቸው፥ ዘለው ይገቡበታል። በጎ አደርጋለሁ ብለው እንዳያበላሹ፥ ከእግዚአብሔርም ፈቃድ ውጪ እንዳይወጡ፥ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር መመካከር፥ አቅማቸውንና ጊዜያቸውን መመዘን ያስፈልጋቸዋል።

## 4.4. "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ያላቸው፥ ራሳቸውን ይረሳሉ

ይሄ ስጦታ ያላቸው አማኞች፥ ለሌላው መጠንቀቅ፥ ለሌላው ማሰብ ባህሪያቸው ነው። ለሌሎች ሲያደርጉ እያጉረመረሙ፥ ወይንም ደስ ሳይላቸው አይደለም። ሊሠሩ የሚችሉ ሌሎች ሰዎች ቢኖሩም፥ ሁልጊዜ "እኔ ልሥራው" የሚሉ

ናቸው። በእንግድነት ሄደው ከበሉና ከጠጡ በኋላ ቁጭ ብለው በመጫወት ፈንታ፥ ብድግ ብለው አንድ ነገር መሥራት ይፈልጋሉ። የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት ለማሟላት ሲሮጡ፥ ስለራሳቸው የሚያስቡበት፥ ለራሳቸው የሚያደርጉበት ጊዜ የላቸውም። ራሳቸውን ችላ ማለታቸውን ቢያውቁም፥ የሚያስደንቀው ደስ ብሏቸው እንጂ እያጉረመረሙ የማይሠሩ መሆናቸው ነው።

### 4.5. "ሌሎችን የማገልገል ስጦታ" ያላቸው፥ ደከመኝን አያውቁም

ሌሎችን ሲረዱ ወይንም ሲያገለግሉ ደስ እያላቸው ስለሆነ፥ "ደከመኝ" ብለው ማቆም አይፈልጉም። ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ አይሉም። የማይደክም ጉልበት አላቸው። *"...የሚያገለግልም ቢሆን እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል"* (1 ጴጥ. 4፥11) የሚለውን የጌታን ቃል በተግባር የሚያውሉ ናቸው። ይሄ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ተወዳዳሪ የሌለው ጉልበት (አቅም) አላቸው፤ እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው አስፈላጊውን የዕንቅልፍ ሰዓት ባያገኙም፥ ደስ ብሏቸው መኖር ይችላሉ። ኃይላቸውና ጉልበታቸው ምድራዊ ሳይሆን፥ ሌሎችን ለመርዳት ወይንም ለማገልገል እንዲችሉ ከጌታ የተሰጣቸው ልዩ ስጦታ ነው። ሌላው እንዲሠራ ሥራውን በማከፋፈል ፈንታ ሁሉንም መሥራት ይፈልጋሉ። ሌላው እንዲሠራ ከጠየቁ "የበደለኛነት" ስሜት ይሰማቸዋል። በተለይ "ቆሻሻውን፥ ዝቅተኛ የሆነውን ሥራ ሌላውን ሰው እንዴት ሥራ እላለሁ?" በማለት ሥራውን ሁሉ ብቻቸውን ለመሥራት ይታገላሉ።

## 5. ሌሎችን የማገልገል ስጦታ ያላቸው፥ አንዳንድ ድካም ይታይባቸዋል

### 5.1. አማኞች ሁሉ እንደእነርሱ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ

ማንኛውም አማኝ የራሱ ድካም እንዳለበት ሁሉ፥ ሌሎችን የማገልገል ስጦታ ያላቸውም አማኞች የራሳቸው የሆነ



ድካም አላቸው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የምትሆነን ታሪኳ በሉቃ. 10፥38-42 የተጻፈው ማርታ ነች። ማርታ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዋ *"ማገልገል"* ስለሆነ፥ በስጦታዋ ጌታ ኢየሱስን ስታገለግለው እይተናል። ማርያም ግን "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ የላትም። የመረጠችው በክርስቶስ እግር ሥር ቁጭ ብላ ማዳመጡን ነው። ማርታ እህቷ ማርያም እንደ እርሷ የአገልግሎት መንፈስ የሌላት በመሆኗ በጣም እንደተበሳጨች እናያለን። ማርያምን ብቻ ሳይሆን፥ ልታስደስተው የምትሞክረውን ኢየሱስንም ወቀሰችው። *"ጌታ ሆይ! እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አያግድህምን?"* አለችው (የሉቃ. 10፥41)። ማርታ ጥሩ ምግብ አዘጋጅታ ለማቅረብ የምታደርገውን ጥረት ኢየሱስ በእርግጥ ያደንቃል። ይሁን እንጂ፥ የነበረባትን መንፈሳዊ ድካም አይቶ ዝም ብሎ ማለፍ ስላልፈለገ፥ *"ማርታ! ማርታ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ፥ ትታወኪማለሽ፥ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው..."* አላት (የሉቃ. 10፥42)። ኢየሱስ ይህን ሲል የማርታ *"የአገልግሎት ስጦታ"* አያስፈልግም ወይም ዋጋ የለውም ማለቱ አልነበረም።

ይሄ ችግር የማርታ ብቻ ሳይሆን፥ በዘመናችንም "ሌሎችን የማገልገል" ስጦታ ያላቸው የአንዳንድ አማኞችም ችግር ነው። የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም አልቆ ሕዝቡ ዳር ቆሞ ቡና እየጠጣ ሲጫወት፥ እርስ በርሱ ሕብረት ሲያደርግ፥ "የማገልገል ስጦታ" ያላቸው ወንዶቹ ወለሉን ሲጠርጉ፥ ወንበር እያጠፉ ሲያነሱ፥ ሴቶቹ ደግሞ ቡና እያፈሉ ሲያስተናግዱ ማየት የተለመደ ነው። የማገልገል ስጦታ ያላቸው አማኞች በየሳምንቱ ይህን ያዩና፥ "ይሄ ሁሉ ሰው እኛ ስንሠራ ለምን ቆሞ ያየናል? ኑና እርዱ ካልተባሉ ለምን ራሳቸው አውቀው አይረዱም?" በማለት እንደ ማርታ ማጉረምረምና ቅሬታቸውን ማሰማት ይጀምራሉ። ስጦታው የሌላቸው ሰዎች እንደእነርሱ መሆን እንደማይችሉ ተገንዝበው ቁጣቸውን መሥመር ማስያዝ

ካልቻሉ፥ በአገልግሎት ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ያጣሉ። ሳያውቁት እንደ ማርታ ነቃፊዎች ይሆናሉ። ይህን ዓይነቱም ጠባይ ክርስቲያናዊ ባህሪ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋቸዋል።

### 5.2. ቤተ ሰባቸውን የመርሳት ዝንባሌ አላቸው

ሌሎችን የማገልገል ስጦታ ያላቸው አማኞች፥ ብዙ ጊዜ እርዳታ ሲጠየቁ "እምቢ! ዛሬ አልችልም! ሌላ ኃላፊነት አለብኝ" ማለት ስለማይችሉ፥ ብዙ ኃላፊነት ውስጥ ራሳቸውን ይከቱና የራሳቸውን ቤት ችላ የማለት ዝንባሌ አላቸው። የኑሮ ጓደኞቻቸው እንደሚገባው ችግራቸውን ካልተረዱላቸው፥ በትዳራቸው ላይ እንቅፋት፥ ወይንም ችግር መፍጠሩ የማይቀር ነው። "እርሱ፥ ወይንም እርሷ ለቤቷ ግድ የላትም" የሚል አስተያየት መስማት ለብዙዎቻችን እንግዳ አይደለም። እቤታቸው ውስጥ ያለውን ሥራ ለመሥራት አለመፈለግ ሳይሆን፥ ጊዜያቸውን የሚሻማባቸው ብዙ ኃላፊነት ውስጥ ስለሚገቡና ጊዜ ስለሚያጥራቸው ብቻ ነው። ቅደም ተከተላቸውን ካላስተካከሉ፥ ከኑሮ ጓደኛቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደሚያሻክርባቸው የታወቀ ነው።

### 5.3. ማገልገል እንጂ፥ መገልገል አይፈልጉም

*"የማገልገል ስጦታ"* ያላቸው አማኞች ለሌሎች ሲያደርጉ፥ ሌሎችን ሲያገለግሉ እንጂ፥ ሌሎች ሲያገለግሏቸው ብዙ ጊዜ ደስ አይላቸውም። ሌሎች ካገለገሏቸው ደካማ የሆኑ መስሎ ይሰማቸዋል። መስጠት እንጂ፥ መቀበል አይሆንላቸውም። መስጠት ብቻ ሳይሆን መቀበልን፥ ማገልገል ብቻ ሳይሆን መገልገልንም መማር አለባቸው። ካልሆነ ሌሎች እነርሱን በማገልገል የሚያገኙትን በረከት እንዳያገኙ ይሆናሉ። ይህን ዓይነቱን ባህሪያቸውን ካላስተካከሉ፥ በመቀበል ውስጥ ያለውንም በረከት ያጣሉ።

☆ ☆ ☆ ☆



ምዕራፍ 15

# የመለገስ ስጦታ

*"...ስጦታችን መለገስ ከሆነ፥ ከልብ እንለግስ..."*
*(ሮሜ 12*8)*

### 1. "የመለገስ ስጦታ" ችላ የሚባል ስጦታ አይደለም

መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ለአማኞች የሚያከፋፍለው ሌላው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ *"የመለገስ ስጦታ"* ነው። *"...እንደ ተሰጠንም ጸጋ፥ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን.... የሚሰጥ በልግስና ይስጥ..." ሮሜ 12፥6፥ 8)።* *"የመለገስ ስጦታ"* ማለት፥ ገንዘብም ሆነ ቁሳቁሳዊ የሆነውን ነገር ሰጪው "ትርፍ ወይም ጥቅም" አገኝበታለሁ ሳይል፥ ለእግዚአብሔር ክብር ሲል በደስታ የመስጠት ችሎታ ማለት ነው። *"መለገስ"* የራስ የሆነውን ገንዘብም ሆነ ጊዜን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲውል በማሰብ ለሌለው ማካፈል ነው። *"የመለገስ ስጦታ"*

ያለው አማኝ የራሱ የሆነውን በልግስናና በደስታ ይሰጣል። መንፈስ ቅዱስ *"የመለገስ ስጦታን"* የሚሰጣቸው ብዙ ገንዘብ ወይንም ሀብት ላላቸው አማኞች ብቻ አይደለም። አነስተኛ ገቢ ያላቸውም አማኞች *"የመለገስ ስጦታ"* ሊኖራቸው ይችላል።

እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለአማኞች የሚ ሰጥበት ዋናው ምክንያት ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት እን ደሆነ መርሳት የለብንም። ይህንን ባለመገንዘብ አልፎ አልፎ አንዳንድ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ገንዘባቸ ውን እንደሚሰጡ እናውቃለን። አንዳንዶቹ ስጦታቸውን ለዓለ ማዊ ድርጅት የሚሰጡት፥ ያሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በገንዘብ ማነስ ምክንያት አገልግሎቷን እንደሚገባው መፈጸም እንዳቃታት እያዩና እያወቁ ነው። ይህን ሲያደርጉ፥ እግዚአብ ሔር የሰጣቸውን ታላቅ ስጦታ ያለቦታው ማዋላቸው እንደሆነ የተረዱት አይመስልም። እነርሱ የሚያዩት "መለገሳቸውን" ብቻ ነው።

*"የመለገስ ስጦታ"* በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታወቀም ባይሆን፥ ከሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ዝቅተኛና የማያስፈልግ ስጦታ አይደለም። አማኞች በልግስና ካልሰጡ፥ መጋቢዎች መመገብ፥ ማስተማር፥ መምራት እንዲሁም ሌሎች በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ የተሰለፉ አገልጋዮች አገልግሎ ታቸውን እንደሚገባው መፈጸም እንደማይችሉ እናውቃለን። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለሁላችንም እንዲሰጠን መለመን የምንችል ከሆነ፥ የጌታን አገልግሎት በገንዘባቸው መደገፍ እንዲችሉ ብዙዎች *"የመለገስ ስጦታ"* መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣቸው ብንጸልይ፥ ጸሎታችን ከመስመር የወጣ አይሆ ንም። ስጦታችን ለእግዚአብሔር መንግሥት ማስፋፊያ እንዲሆን እንጂ፥ እግዚአብሔር ሥራችንን እንዲባርክና ባለጸጋ እንዲያደ ርገን ብለን ለእግዚአብሔር የምንሰጠው *"ጉቦ"* አይደለም። እግዚአብሔር "መስጠታችንን" ብቻ ሳይሆን፥ በምን ዓይነት



መንፈስ ተነሳስተን እንደምንሰጥ፥ የልባችንን አቋም ያያል። ስጦታ የምንሰጠው ስማችን በወርቅ ቀለም እንዲጻፍ፥ ታሪካችን በጋዜጣ ተጠቅሶ እንዲወራ፥ የቦርድ አባል እንድንሆን፥ ወይንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ምሰሶ እንድንታይና የፈለግነውን ዓይነት ውሳኔ ማስተላለፍ እንድንችል ከሆነ፥ ስጦታችን በእግዚ አብሔር ዘንድ ፈጽሞ ዋጋ የለውም። "የመስጠት ስጦታችን ንም" እንደሚገባው እንዳልተጠቀምንበት ግልጽ ነው።

"ስጦታችንን" በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ እንዳይኖረው ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል አንደኛው የተሳሳተ ዓላማ ኖሮን የምንሰጠው ስጦታ ነው። ደስ ሳይለን፥ ወይንም ተገት ጉተን የምንሰጠው ስጦታ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ዋጋ የለውም። ጳውሎስ በምን ዓይነት መንፈስ "መስጠት" እንዳለብን ሲናገር *"ጥቂት የዘራ ጥቂት መከር ይሰበስባል፤ ብዙ የዘራ ብዙ መከር ይሰበስባል የሚለውን ቃል አስታውሱ። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚወድደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለ ሆነ እያንዳንዱ ለመስጠት የፈለገውን በልቡ ፈቅዶ በደስታ ይስጥ እንጂ እየተጸጸተ ወይም በግዴታ አይስጥ"* ይላል (2 ቆሮ. 9፥6-7)። በማመንታት፥ በግዴታና በማጉረምረም መስጠት፥ የአማኙ ልብ ምን ዓይነት እንደሆነ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት የማያገኝ እንደሆነ ተመልክ ተናል።

በምን ዓይነት ሁኔታና መንፈስ መስጠት እንዳለብን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ራሱ ሲያስተምር፥ *"ስለዚህ አንተ ለድኻ በምት መጸውትበት ጊዜ ግብዞች ከሰዎች ምስጋና ለማግኘት ብለው በየምኩራቡና በየመንገዱ እንደሚያደርጉት ለታይታ አታድርግ። በእውነት እላችኋለሁ እነርሱ ዋጋቸውን በቅድሚያ አግኝተዋል። አንተ ግን ለድኻ በምትመጸውትበት ጊዜ ቀኝ እጅህ የሚሰጠ ውን ግራ እጅህ እንኳ አይወቅ። ምክንያቱም ምጽዋትህ በስውር*

*መሆን አለበትI በስውር የተሠራውን የሚያይ አባትህም የመልካም ሥራህን ዋጋ ይከፍልሃል"* ይላል (የማቴ. 6÷2-4)። ስጦታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንዲያገኝ÷ በትዕቢትና በወግ አጥባቂነት ሳይሆን÷ በትህትናና በደስታ መስጠት አለብን። የምንሰጠው ለጋስ ለመምሰል÷ ሰዎች እንዲያዩልን ከሆነ÷ *"የመለገስ ስጦታችንን"* በተግባር ላይ አላዋልንም።

አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን እንዲለማመዱ÷ ወይም በሥራ ላይ እንዲያውሉ የምናደፋፍራቸው ከሆነ÷ *"የመለገስ ስጦታ"* ያላቸውንም ስጦታቸውን እንደሚገባው እንዲለማመዱ ከመምከርና ከማደፋፈር ወደ ኋላ ልንል አይገባም። ለአስተማሪዎችና ለመጋቢዎች *"የመሪዎች ሥልጠና"* እያልን ሴሚናር የምናዘጋጅ ከሆነ÷ አማኞችን ስለ ገንዘብና ስለ መስጠት ማስተማር የማንደፍርበት ምክንያቱ ምን ይሆን? ስለ ገንዘብ አማኞችን ማስተማር የማንደፍረው ምናልባት "ገንዘብ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው" በማለት ይሆን? ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ *"የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው"* ይላል እንጂ÷ "ገንዘብ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው" አይልም (1ኛ ጢሞ. 6÷10)። *"የመለገስ ስጦታ"* ያላቸውን በመስጠታቸው እንዲተጉ ማደፋፈር መንፈሳዊ እንጂ÷ ሥጋዊ አሳብ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ "የመለገስ ስጦታ" ያላቸውን ለመምከር እንዲህ ሲል ጽፏል። *"የዚህ ዓለም ሀብታሞች እንዳይታበዩ ወይም ተስፋቸውን በሚጠፋ ሀብት ላይ እንዳያደርጉ እዘዛቸውI እንዲሁም ተስፋቸው እኛን ደስ እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን እዘዛቸው። ደግሞም መልካም ሥራ እንዲሠሩ በመልካም ሥራ ሀብታሞች እንዲሆኑ ለመለገሥና ያላቸውንም ለማካፈል ዝግጁዎች እንዲሆኑ እዘዛቸው። በዚህ ዐይነት እውነተኛውን ሕይወት ለማግኘት መሠረቱ ጽኑ የሆነውን ሀብት በሚመጣው ዘመን ለራሳቸው ያከማቻሉ"* (1ኛ ጢሞ. 6÷17-19)።



ማንኛውም አማኝ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከገንዘቡ የተወሰነውን መስጠት እንዳለበት እናውቃለን። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለ መስጠት ሲጽፍላቸው÷ *"እኔ በምመጣበት ጊዜ የገንዘብ መዋጮ እንዳይደረግ በየሳምንቱ እሑድ ከእናንተ እያንዳንዱ በሚያገኘው ገቢ መጠን እያዋጣ ለይቶ ያስቀምጥ"* አላቸው (1ኛ ቆሮ. 16÷2)። እንዲሁም በሉቃስ 12÷48 ላይ *"ብዙ ከተሰጠው ሰው÷ ብዙ ይፈለግበታልI ብዙ ዐደራም ከተሰጠው ሰው ብዙ ይጠበቅበታል"* ይላል (የሉቃ. 12÷48)። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ *"የመለገስ ስጦታ"* የነበራቸውን አማኞች በመስጠታቸው እንዲተጉ ለማደፋፈር በመቄዶንያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህል በስጦታቸው ይተጉ እንደነበረ ምሳሌነታቸውን ይጠቅሳል። *"እነርሱ ብዙ መከራና ፈተና ደርሶባቸዋልI ይሁን እንጂ ደስታቸው ታላቅ ስለሆነ ምንም እንኳ በጣም ድኾች ቢሆኑ ከፍ ያለ ልግስና አድርገዋል። የሚችላቸውን ያህል ብቻ ሳይሆን ከሚችላቸውም በላይ በፈቃደኝነት እንደሰጡ እኔ እመሰክርላቸዋለሁI በይሁዳ ያሉትን ክርስቲያኖች የመርዳት ዕድል እንዳይነፈጋቸውም አጥብቀው ለመኑንI እነርሱ ያደረጉት እኛ ከጠበቅነው በላይ ነውI በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡI ቀጥሎም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጥተዋል"* (2 ቆሮ. 8÷2-5)። ስለ መቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ከነገራቸው በኋላ÷ እነርሱም ማድረግ ያለባቸውን እንዲያደርጉ አደፋፈራቸው። *"በዚህ ጉዳይ ለእናንተ መልካም መስሎ የታየኝን ምክር እሰጣችኋለሁI ባለፈው ዓመት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ የፈለጋችሁት እናንተ ነበራችሁ። ስለዚህ የመስጠት ፈቃደኝነታችሁ አሳብ በሥራ ላይ ውሎ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ ባላችሁ መጠን ያንን ያሰባችሁትን አሁን አድርጉ። ለመስጠት*

*ባለው መጠን ሲሰጥ እንጂ በሌለው መጠን ሲሰጥ አይደለም"* አላቸው (2 ቆሮ. 8፥10-12)። አንዳንዶቻችን ማስተማር፣ መስበክ፣ የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት፣ በእጆቻችን ሠርተን ቅዱሳንን ማገልገል አንችልም ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር በገንዘብ ባርኮን እንደሆነ፥ ለእግዚአብሔር ሥራ በመስጠት የአገልግሎት ድርሻ ሊኖረን ይችላል። ባንሰብክም፥ የሚሰብኩትን በገንዘብ መርዳት ከቻልን በእግዚአብሔር ፊት ከሚሰብኩት እኩል ሽልማት ይኖረናል።

## 2. *አሥራቱን የሚከፍል ሁሉ፥ "የመለገስ ስጦታ" አለው ማለት አይደለም*

ማንኛውም ክርስቲያን ከገቢው አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት እንዳለበት እናውቃለን። እንደ እግዚአብሔር ቃል፥ ለእግዚአብሔር መስጠት ያለባቸው "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፥ አማኞች ሁሉ ናቸው። *"እግዚአብሔር የሚወደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለሆነ እያንዳንዱ ለመስጠት የፈለገውን በልቡ ፈቅዶ በደስታ ይስጥ እንጂ እየተጸጸተ ወይም በግዴታ አይስጥ"* ይላል (2 ቆሮ. 9፥7)። *"እያንዳንዱ"* ሲል፥ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፥ አማኞች ሁሉ መስጠት እንዳለባቸው ሲገልጽ ነው። ሀብታም ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ድሃ የሆኑ ክርስቲያኖችም እንደ አቅማቸው መስጠት አለባቸው። አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በተለያየ አቅጣጫ ማደግ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ፥ በመስጠት ውስጥ ያለውን በረከት ለማግኘት፥ "በመስጠትም" ማደግ አለባቸው።

ለእግዚአብሔር ካለን ውስጥ ምን ያህሉን መስጠት አለብን? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። አሥራት ማለት ከመቶ አሥር (10%) ወይንም "አንድ አሥረኛ" ማለት ነው። ማንኛውም ክርስቲያን መስጠት ያለበት ዝቅተኛው፥ "አንድ አሥረኛ"



እንደሆነ እናውቃለን። አሥራታቸውን መክፈል የማይፈልጉ አንዳንድ አማኞች ምክንያት የሚሰጡት፥ "መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *"አሥራት"* የሚል ቃል የለም" በማለት ነው። ይሄ አጥጋቢ ምክንያት አይመስለንም። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *"ሥላሴዎች"* የሚል ቃል አናገኝም። ስለሆነም፥ "በሥላሴዎች አናምንም" አንልም። ልክ እንደዚሁ "አሥራት" የሚል ቃል ስለሌለ "አሥራት በመክፈል አላምንም" ልንል አይገባም።

ከአንድ አሥረኛ በታች የሚሰጥ አማኝ ቢኖር፥ እግዚአብሔርን እየሰረቀ፥ ወይንም እየዋሸ እንደሆነ ማወቅ አለበት። እኔና እናንተ በተለያየ መንገድ፥ ለመንግሥት መክፈል ያለብንን ቀረጥ አሳንሰን መክፈል እንችላለን። ሰውን በተለያየ አቅጣጫ መዋሸት እንችላለን፤ እግዚአብሔርን ግን መዋሸት አንችልም። *"ራሳችሁን አታታልሉ፤ በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ አይቻልም፤ ምክንያቱም ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነው"* ይላል (ገላት. 6፥7)። ብዙዎቻችን ለእግዚአብሔር የሚገባውን እንደሚገባው አንሰጥም። በአሜሪካ ያሉት ክርስቲያኖች በዓመት የሚሰጡት መካከለኛው (አቨሬጅ) ስጦታ $145 ብቻ እንደሆነ ታውቋል። ይህን ስጦታ ሲሰጡ "የዓመት ገቢያችን $1,450 ነው" ማለታቸው ነው። ይሁን እንጂ፥ ይሄ ፍጹም ከእውነት የራቀ እንደሆነ ግልጽ ነው። አንድ ጸሐፊ ብዙ ሀብታሞች ያሉበት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናኑ ስለሚሰጠው የገንዘብ መጠን ሲናገሩ፥ "እነዚህ ሀብታም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በዓመት የሚያገኙት ገቢ ቀርቶ "ለድኩማን የሚሰጠው አነስተኛ ገንዘብ" (*welfare payments*) ቢያገኙ፥ ከዚያ ገቢያቸው ውስጥ ሁሉም አሥራታቸውን፥ ማለትም አንድ አሥረኛውን በትክክል ቢከፍሉ፥ አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምትሰበስበው ገንዘብ 40% (አርባ ከመቶ) የበለጠ እንደሚሆን" ተናገሩ። ይህን ሲሉ አሥራታቸውን በትክክል የሚከፍሉት በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ መግለጻቸው ነው።

ፕሬዚደንት ካርተር ክርስቲያን እንደሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ እንደነበሩ ብዙዎቻችን እናውቃለን። የአሜሪካ ፕሬዚደንት በነበሩበት ወቅት የዓመት ንጹህ ገቢያቸው $122,189 ነበር። ከዚህ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጡት፥ $6,000 ብቻ ሲሆን፥ ይሄም 4.9% (ከመቶ አራት ነጥብ ዘጠኝ) ነው። ይሁን እንጂ፥ ከፕሬዝደንት ኒክሰን በጣም ይሻላል። ፕሬዚደንት ኒክሰን ለቤተ ክርስቲያን በዓመት ውስጥ የሰጡት $250 ብቻ ነበር። እኛስ ምን ያህል እንሰጥ ይሆን? ሂሳብ መርማሪ (ኦዲተር) ቢላክብን፥ ብዙዎቻችን የጌታን ገንዘብ እኪሳችን እንደምናስቀር ይረጋገጥብን ነበር። ለጌታ የሚገባውን ገንዘብ ሳያስቀሩ፥ እንዲያውም ከአሥራታቸው በላይ የሚሰጡትን እግዚአብሔር በቃሉ በገባው ተስፋ መሠረት የበረከቱን ዝናብ ያወርድላቸዋል። *"ስጡ ለእናንተም ይሰጣችኋል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ እንዲሁ ይሰፈርላችኋል፤ እንዲያውም በጥሩ መስፈሪያ ታምቆና ተጠቅጥቆ እስኪትረፈረፍ ድረስ ተሰፍሮ ይሰጣችኋል"* (የሉቃ. 6፥38) ይላል።

አሥራታቸውን በታማኝነት የሚሰጡ ሁሉ "የመለገስ ስጦታ" አላቸው ማለት አይደለም። ማንኛውም ክርስቲያን አሥራቱን ሲሰጥ፥ እንደ ክርስቲያን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መፈጸሙ ነው። የአሜሪካ መንግሥት ከሕዝቡ ቀረጥ የሚሰበስበው "ከመቶ እጅ" (ፐርሰንቴጅ) ይሁን እንጂ፥ የሁሉም አንድ ዓይነት ወይንም "ፍላት ታክስ" *(flat tax)* አይደለም። ወሳኙ የእያንዳንዱ ሰው የገቢ መጠን ነው። ደሞዛቸው ከፍ ያለው፥ የሚከፍሉት ቀረጥ "ፐርሰንቴጅ" ከፍ ይላል። ክርስቲያኖችም አሥራታችንን ስንከፍል ከመቶ አሥር ከማለት ይልቅ፥ በገቢያችን መጠን የምንከፍለውም ከፍ ማለት እንደሚገባው ማመን ያስፈልገናል። ይህንን የተረዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች ለጌታ ሥራ ሲሰጡ ከመቶ አሥሩን ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያ በላይ የሆን



ውን ነው። "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው አማኞች፥ ምን ያህል መስጠት አለብኝ ብለው አይጠይቁም። ለሚሰጡት ስጦታ ሌላ መመሪያ አላቸው። "ለጌታ ምን ያህሉን ልስጠው?" ብለው በመጠየቅ ፈንታ፥ "ጠቅላላው ገንዘቤ የጌታ ስለሆነ፥ ከጌታ ገንዘብ ምን ያህሉን ለራሴ ላስቀር?" ብለው ይጠይቃሉ። "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው አንዳንድ አማኞች 90% ለጌታ ሰጥተው፥ ለራሳቸው 10% ያስቀራሉ። የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው እንዲህ ዓይነት ለጋሥ የሆኑ ጥቂት ሰጪዎች በሚሰጡት ስጦታ ነው። ብዙዎች ግን ሌላው ቀርቶ መስጠት ያለባቸውን አንድ አሥረኛውን እንኳን በትክክል አይሰጡም። ክርስቲያኖች ሁሉ አሥራታቸውን የሚከፍሉ ቢሆን ኖሮ፥ የወንጌል ሥርጭት በተፋጠነ መንገድ ለዓለም በአጭር ጊዜ ውስጥ ይደርስ ነበር።

### 3. "ድሃዋ መበለት "የመስጠት ስጦታ" ነበራት

በአዲስ ኪዳን የመስጠት ስጦታ ከነበራቸው ሰዎች መካከል ጎልታ የምትታየው "ድሃዋ መበለት ናት። *"አንዲት ድሃ መበለትም መጥታ ሁለት ሳንቲም የሚያህል የናስ ገንዘብ ሰጠች። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ በእውነት እላችኋለሁ፤ በሣጥን ውስጥ ገንዘብ ከጨመሩት ሰዎች ሁሉ አብልጣ የሰጠች ይህች ድሃ መበለት ናት፤ ምክንያቱም ሌሎቹ ሁሉ የሰጡት ካላቸው ሀብት የተረፋቸውን ነው፤ እርስዋ ግን ድሃ ሆና ሳለች ምንም ሳታስቀር ያላትን ሁሉ ሰጠች" (ማር. 12፥42-44)።* ያቺ ድሃ መበለት ሁለት ሳንቲም የሰጠችው፥ ስጦታዋ በሰው ዘንድ እንዲታይላት፥ በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት አይደለም። ሁለት ሳንቲም፥ የሚያከራት፥ በሰው ዘንድ እንድትታይ የሚያደርጋት ስጦታ እንዳልሆነ እናውቃለን። በዚያ ስብሰባ ውስጥ የሰጠችውን ስጦታ አይቶ ያደነቀ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ሰው አልነበረም። ለራሷ ምንም ሳታስቀር፥ ያላትን ሁሉ የሰጠችው፥ እውነተኛ የሆነ

የጌታ ፍቅር በልቧ ውስጥ ይቃጠል ስለነበረ ነው። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 9፥7 ላይ *"እግዚአብሔር የሚወድደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለሆነ፥ እያንዳንዱ ለመስጠት የፈለገውን በልቡ ፈቅዶ በደስታ ይስጥ እንጂ እየተጸጸተ ወይም በግዴታ አይስጥ"* የሚለው ሀሳብ የገባት ሴት ትመስላለች። ስለዚህ የሰጠችው በደስታ እንጂ እያጉረመረመች አልነበረም። በክርስቶስ ዓይን ስጦታዋን "ታላቅ" ያደረገው በፍቅር ተሞልታ የሰጠች በመሆኗ ነው። ሁለት ሣንቲም ብዙ ገንዘብ አይደለም፤ በፍቅር በተሞላ ልብ ሲሰጥ ግን፥ ዋጋው በጌታ ፊት እጥፍ ድርብ ይሆናል። ኢየሱስ ያቺ ድሃ መበለት "ሌሎች ሁሉ ከሰጡት ስጦታ አብልጣ ሰጠች" በማለት ስጦታዋን ያደነቀው፥ ስጦታዋን ሰዎች በሚቆጥሩት ዓይነት ቆጥሮ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

"የመለገስ ስጦታ ያላቸው" ስጦታ የሚሰጡት በማንም ግፊት ወይንም ማባበል አይደለም። ያቺ ድሃ መበለት ስትሰጥ ለራሷ ምንም አላስቀረችም ነበር። ያላትን ሁሉ፥ ምንም ሳታስቀር እንድትሰጥ ማንም የገፋፋትና ያባበላት ሰው አልነበረም። በራሷ ፈቃድ የሰጠችው ስጦታ ነው። በሐዋርያት ዘመን የነበሩት ሐናንያና ሰጲራ ስጦታቸው እግዚአብሔርን አስቆጥቶት እንደ ነበረ እናስታውሳለን። እግዚአብሔር የተቆጣው ስጦታቸው አነሰ ብሎ ሳይሆን፥ ግማሽ ልብ ሆነው በመስጠታቸው ነበር። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ *"ሐናንያ ሆይ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንድትዋሸና ከመሬቱም ሽያጭ ከፊሉን እንድታስቀር ያደረገህ ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ? ሳትሸጠው በፊት መሬቱ የአንተ አልነበረምን? ከሸጥከውስ በኋላ ገንዘቡ የአንተ አልነበረምን? ታዲያ ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም"* አለው (የሐዋ. 5፥3-4)። የዚያች ድሃ መበለት ስጦታ በክርስቶስ ዓይን ሲታይ "ታላቅ" ሆኖ የታየው፥ ስጦታዋ "መስዋዕትነት" ያለበት ስለ ሆነ ነው። አንዳንዶቻችን ግን እንኳን የራሳችን



የሆነውን ለመስጠት ቀርቶ የእግዚአብሔር የሆነውንም መስጠት እያቃተን ነው። ከገቢያችን አንድ አሥረኛው፥ የእግዚአብሔር እንጂ፥ የራሳችን አይደለም። *"በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቴን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በዚህ ፈትኑኝ"* ይላል (ሚል. 3፥10)። አሥራታችንን ለጌታ ሥራ ስንሰጥ፥ የራሱ የሆነውን ሰጠን እንጂ፥ ከራሳችን አጉድለን መስጠታችን እንዳልሆነ ብዙዎቻችን የተረዳነው አይመስልም።

ብዙዎች ለእግዚአብሔር "ስጦታን" ይሰጣሉ፤ የሚሰጡት ግን *"ትራፊያቸውን"* እንጂ፥ ከዋናቸው አጉድለው አይደለም። አንዳንዶቹ ደግሞ የሚሰጡት ሁልጊዜ ሥርዓት ጠብቀው ሳይሆን፥ ደስ ሲላቸው አልፎ አልፎ ትንሽ ጣል ያደርጋሉ። ለሰው ብለው የሚሰጡም አሉ። አንዳንዶቹ ታዋቂ የሆነ ሰው ካልጠየቃቸው አይሰጡም። አሥራታቸውን ሲሰጡ ለመጋቢው ደሞዝ የሚከፍሉ መስሎ የሚሰማቸውም አሉ። መጋቢው ካስቀየማቸው፥ አሥራታቸውን መስጠት ያቆማሉ። አንዳንዶች ደግሞ ስሜታቸው ሲቀሰቀስ ብቻ፥ ማለትም ደስ ሲላቸው ብቻ የሚሰጡ አሉ። በመስጠታቸው ብቻ የቤተ ክርስቲያን "ምሰሶ" የሆኑ ስለሚመስላቸው፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረገው የውሳኔ አሰጣጥ ላይ "የእኔ ሀሳብ ብቻ ይፈጸም" የሚሉ አሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንዳንድ ነገር ቅር ብሏቸው ሲያኮርፉ፥ አሥራታቸውን መስጠት የሚያቆሙም አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ "አሥራታቸውን" ማስፈራሪያ፥ ወዳጅ ማፍሪያ ያደርጉታል። በዚህ ዓይነት መንፈስ የምንሰጠው ስጦታ፥ ምንም ያህል ብዙ ቢሆን፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የለውም። ስጦታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንዲኖረው ከፈለግን፥ ከልባችን፥ እንዲሁም ደስ ብሎን መስጠት ይገባናል።

## 4. "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው ሰዎች መለያቸው (Characteristic) ምንድነው?

### 4.1. ገንዘባቸውን፥ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በነጻ ይሰጣሉ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ከአማኞች መካከል "የመለገስ
ስጦታ" ያላቸውን በቀላሉ ማወቅ ያስቸግራል። ዋናው ምክንያት
*"...ቀኝ እጅህ የሚሰጠውን ግራ እጅህ እንኳን አይወቅ"*
(የማቴ. 6፥3) ስለሚል ይሆናል። *"የመለገስ ስጦታ"* ያለው
አማኝ፥ በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፍ ቢሆንም፥ በል
ግስናው ፍጹም የተለየ ነው። *"የመለገስ ስጦታ"* ያላቸው አማ
ኞች የሚሰጡት፥ ገንዘብ ብቻ አይደለም፤ ጊዜያቸውን፥ ጉልበ
ታቸውንም ይሰጣሉ። የሚሰጡት "ብሰጥ ትርፍ አገኛለሁ፥ ወይም
የበለጠ ይሰጠኛል" በማለት ጥቅም ፈልገው አይደለም። በዚህ
ዓይነት መንፈስ እንዲሰጡ የሚገፋፉና የሚያስተምሩ "የብልጽ
ግና ወንጌል" አስተማሪዎች በዘመናችን ብዙዎች ናቸው።
"የመለገስ ስጦታ" ያላቸው ሲሰጡ ሸርፈው ሳይሆን፥ በሙላት
ነው። የሚሰጡት፥ በሰዎች ዘንድ እንዲጨበጨብላቸው በመፈለግ
አይደለም። ያላቸው ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ስለሚያምኑ፥
የእግዚአብሔርን መልሶ ለራሱ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው
ስለሚሰማቸው ነው።

### 4.2. ማንም ሳያውቅ መስጠት ደስ ይላቸዋል

"ይህን አደረግሁ" ብለን የምንሠራውን ሥራ እንዳናውጅ
የክርስቶስ ፍላጎት ነው። *"ሰዎች ይዩልን ብላችሁ መልካም
ሥራችሁን በሰው ፊት ከማድረግ ተጠንቀቁ። አለበለዚያም
በሰማይ ካለው አባታችሁ ምንም ዋጋ አታገኙም"* (የማቴ.
6፥1) የሚለውን የክርስቶስን ቃል "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው
አማኞች አጥብቀው ይከተላሉ። ስለዚህ "የመለገስ ስጦታ" ያላ
ቸው፥ ምን ጊዜም የሚያደርጉትን በጎ ነገር መናገር አይፈል
ጉም። በሚያደርጉት በጎ ነገር ማስደሰት የሚፈልጉት ሰማያዊ



አባታቸውን እንጂ፥ ሰዎችን አይደለም። ስለሚያደርጉት "ስጦታ"
ማንም ሰው እንዳያውቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ተማሪ
በነበርኩበት ዘመን ከማን እንደተላኩ እስከ ዛሬ ያላወቅኋቸው
ብዙ ስጦታዎችን ተቀብያለሁ። እኔ ባላውቃቸውም፥ እግዚአብ
ሔር ስለሚያውቃቸው፥ እንደ ባለጸግነቱ መጠን አብዝቶ እንደ
ሚባርካቸው አልጠራጠርም። "የመለገስ ስጦታ" ያላቸው ሲሰጡ
ማንም እንዲያውቅባቸው ስለማይፈልጉ ሲሰጡ፥ "ስሜ እንዳይ
ጠቀስ" በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ነው።

### 4.3. በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ

"የመለገስ ስጦታ" ያላቸው አማኞች ለመስጠት ሲሉ ብቻ
ዝም ብለው አይሰጡም። የሚሰጡት፥ ጌታ የሚከብርበትን ሥራ
ይሠራሉ፤ ነፍሳት የሚድኑበትን አገልግሎት ይፈጽማሉ ብለው
ለሚያምኗቸው "መንፈሳዊ አገልግሎቶች" ብቻ ነው። ገንዘባቸ
ውን ሰጥተው መቀመጥ ብቻ ሳይሆን፥ በአገልግሎቱ ውስጥ
ሌላ ዓይነትም ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። ለአገልግሎቱ
ይጸልያሉ፤ ደብዳቤም እየጻፉ ያበረታታሉ።

### 4.4. ስጦታቸው በትክክለኛው ጊዜና ሰዓት፥ ሲደርስ ደስ ይላቸዋል

*"የመለገስ ስጦታ"* ያላቸው አማኞች፥ ስጦታቸውን ዝም
ብለው መጣል አይፈልጉም። መንፈስ ቅዱስ ዕርዳታቸው ወደ
ሚያስፈልገው ሰውም ሆነ መንፈሳዊ ድርጅት፥ በትክክለኛው
ጊዜና ሰዓት እንዲደርስ እንዲመራቸው ይፈልጋሉ። መንፈስ
ቅዱስ መርቷቸው የሚሰጡት ስጦታ የበለጠ ፍሬ እንዳለው
ያውቃሉ። ገንዘባቸውን የሚሰጡት ሰው "እንደሚያስፈልገኝ
በምን አወቅህ?" ብሎ ሲጠይቃቸው ደስ ይላቸዋል። በዚህም
በትክክለኛው ሰዓት ወደ ትክክለኛው ሰው መንፈስ ቅዱስ መር

ቷቸው እንደሰጡ ይገነዘባሉ። *“የመለገስ ስጦታ”* ያላቸው አማኞች መንፈስ ቅዱስ መርቷቸው እንጂ፥ ሰው ጎትጉቷቸው መስጠት አይፈልጉም።

### 4.5. አሥራታቸውንና ከዚያም በላይ በመክፈል ያምናሉ

*“የመለገስ ስጦታ”* ያላቸው፥ ከአሥራታቸው ትንሽም ቢሆን ወደራሳቸው አያስቀሩም። ይህን ቢያደርጉ፥ እግዚአብሔርን እንደ ሠረቁ መስሎ ይሰማቸዋል። ያላቸው ሀብትና ንብረት፥ ይኸውም ቤታቸው፥ መኪናቸው፥ ዕቃቸው የእግዚአብሔር ነው ብለው ያምናሉ። ራሳቸውን የሚያዩት የእግዚአብሔር ንብረት ጠባቂዎች እንደሆኑ አድርገው ነው። *“የመለገስ ስጦታ”* ያላቸው አማኞች የሚሰጡት የተለመደውን አንድ አሥረኛውን፥ ወይንም አሥራታቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ሃያ እና ሠላሳ ከመቶ (20% እና 30%) ነው። እግዚአብሔር በሀብት ከባረካቸው ሀብታም ክርስቲያኖች መካከል 95% (ዘጠና አምስት ከመቶ) ለእግዚአብሔር የሚሰጡ አሉ። እነርሱ የሚወስዱት 5% (አምስት ከመቶ) ብቻ ነው።

ያላቸው ሀብት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው ብለው ስለሚያምኑ፥ የነርሱ ኃላፊነት እርሱ በሚመራቸው መስመር ማከፋፈል ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። የሚሰጡት ነገር ቢያልቅባቸው፥ እግዚአብሔር በጎደለው ላይ እንደሚሞላ ይታመኑበታል። *“አምላኬ እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል”* (ፊል. 4፥19) የሚለ ውን ተስፋ አጥብቀው ይይዛሉ። ለእግዚአብሔር ታዛዦች ከሆኑ፥ የእነርሱን ፍላጎት (ጉድለት) እንደሚያሟላ እምነት አላቸው። የሚያስደንቀው ነገር ለጋስ ሰጪዎች፥ ኃይለኛ ሠራ ተኞች ናቸው።

☆ ☆ ☆ ☆



ምዕራፍ

16

# የማስተዳደር ስጦታ

*“...ስጦታችን ማስተዳደር ከሆነ፥*
*በትጋት እናስተዳድር...”* (ሮሜ 12፥8)

### 1. “የማስተዳደር ስጦታ” ምንድነው?

በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያናቸው ምን ዓይነት አቋም ላይ እንደሆነች፥ ዓላማዋ ምን እንደሆነ፥ ምን ዓይነት ብርታትና ድካም እንዳላት አያውቁም። ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትመራበት ግልጽ የሆነ መመሪያ የላትም። እረኛ የሌላቸው በጎች፥ እንዲሁም መሪ የሌላቸው ተከታዮች ምን ያህል የተቅበዘበዙ እንደሚሆኑ የሚያውቀው ጌታ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ያለመሪ እንዳትሆን፥ *“የማስተዳደር ስጦታን”* የክርስቶስ የአካል ክፍሎች ለሆኑት አንዳንድ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ያከፋፍላል።

*"ማስተዳደር"* የሚለው ቃል የመጣው፥ *"ኩበርኔሲስ"* (kuberneseis) ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ቀጥተኛ ትርጉሙ *"የመርከብ መሪ፥ ወይም ገዢ"* ማለት ነው። ይህ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራ ተጠቅሶ የምናየው፥ በዓለም ውስጥ ያለውን *"መሪ፥ ገዢ"* የሚለውን አሳብ ይዞ ነው። ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር *"...የማስተዳደር ችሎታ ያላቸውን..."* (1 ቆሮ. 12፥28) ሲል፥ ዓለማዊውን *"የአስተዳደር ችሎታ"* ሳይሆን፥ መንፈሳዊ የሆነውን መጥቀሱ ነው። *"አስተዳዳሪ"* ስንል፥ የመምራት ወይንም የማስተዳደር ችሎታ ያለውን ሰው መጥቀሳችን ነው። ይህን ስጦታ "ከመጋቢው" አገልግሎት ጋር አጣምሮ ማየት፥ በብዙዎች ዘንድ አከራካሪ ወይንም አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። ይኸውም "በመጋቢነት" የሚያገለግሉ ሁሉ *"የማስተዳደር ስጦታ"* ሊኖራቸው ይገባል የሚል አሳብ ስለሚነሳ ነው። ይሁን እንጂ፥ *"የማስተዳደር ስጦታ"* ሳይኖራቸው መጋቢ መሆን እንደሚችሉ እናምናለን።

*ፒተር ዋግነር* "የማስተዳደር ስጦታ" ምን እንደሆነ ሲገልጹ፥ *"የማስተዳደር ስጦታ፥ እግዚአብሔር ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የሚኖራትን የቅርብና የሩቅ ዓላማ የመረዳት፥ እንዲሁም ልትደርስበት ካሰበችው ግብ እንድትደርስ ያቀደችውን ዕቅድ በአግባቡ የማስፈጸም ችሎታ ሲሰጣቸው ነው"* አሉ። *"ማስተዳደር"* የሚለው ቃል፥ *"ኩበርኔሲስ"* (kuberneseis) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ፥ ትርጉሙም *"የመርከብ መሪ"* እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። የመርከብ መሪ፥ መርከቧ ከየት ተነስታ የት እንደምትደርስ፥ የጉዞዋ ዓላማ ምን እንደሆነ ወሳኝ ነው። መርከቡ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ወይም መርከበኞች ትዕዛዝ የሚቀበሉት ከመርከቡ መሪ (ካፒቴን) ነው። በባሕር ላይ እያሉ



መርከቧ አንድ ዓይነት ችግር ቢገጥማት፥ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ወሳኙ የመርከቡ መሪ ነው። ልክ እንደዚሁ፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያንም በምታደርገው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መሪ መሆን የሚችሉት፥ እግዚአብሔር ራሱ በመሪነት ያስቀመጣቸው ሰዎች ብቻ መሆን አለባቸው። እግዚአብሔር *"የማስተዳደር ስጦታ"* የሰጣቸው መሪዎች፥ ልክ እንደ "መርከብ መሪ" (ካፒቴን) የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ዕድገቷን እንዲያፋጥኑ ኃላፊነትን ከእግዚአብሔር ተቀብለዋል። "የማስተዳደር ስጦታ" ወይንም ጥሪ የሌላቸው "የቤተ ክርስቲያን መሪዎች" የመሪነትን ሥፍራ ሲይዙ፥ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ፊት በማስኬድ ፈንታ ወደ ኋላ ይጎትቷታል።

ጳውሎስ *"... በትጋት እናስተዳድር"* ሲል፥ *"ሥልጣንን ወይንም ደረጃ"* መጥቀሱ ሳይሆን፥ *"ስጦታን"* ነው። *የአስተዳደር ስልጣንና የአስተዳደር ስጦታ፥* ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። ስለዚህ በማስተዳደር "ስልጣን" ላይ የተቀመጡ ሁሉ *"የማስተዳደር ስጦታ"* አላቸው ማለት አይደለም። በመጋቢነት የሚያገለግለው ሰው *"የማስተዳደር ስጦታ"* ቢኖረው፥ አገልግሎቱን የበለጠ ፍሬያማ እንደሚያደርግለት ግልጽ ነው። ቤተ ክርስቲያን በሥርዓት እንድትሄድ፥ እንደሚገባው እንድታድግ፥ ሥርዓት ያለው አስተዳደር እንዲኖራት ያስፈልጋል። ስለዚህ መጋቢው *"የማስተዳደር ችሎታ"* ከሌለው፥ ወይንም ጊዜ ወስዶ በአስተዳደር ትምህርት ራሱን ካላዘጋጀ፥ ይህንን ቀዳዳ መድፈን የሚችል ከምዕመናኑ፥ ወይንም ከመሪዎች መካከል ማን ነው? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ አማኝ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲችል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተሰጠው ስለሆነ፥ ከመሪዎች ወይም ከምዕመናኑ መካከል *"የማስተዳደር ስጦታ"* ያላቸውን በማስተዳደር አገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል። በተለይ ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን

አገልግሎት ሲሾሙ፣ ወይንም ሲመረጡ፣ "የማስተዳደር ስጦታ" እንዳላቸው መመልከት ይጠቅማል።

## 2. ሥራንና ኃላፊነትን ለሌሎች ማከፋፈል (delegation)፣ የአስተዳደር ችሎታን ይጠይቃል

ጥሩ የአስተዳደር ሥርዓት አስፈላጊነቱ የታመነበት፣ በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ ጥንት የእስራኤል ሕዝብ በበረሃ ጉዞ ውስጥ በነበረበትም ዘመን ነው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ በበረሃ ውስጥ ሲመራ፣ በቂ የአስተዳደር ችሎታ ስላልነበረው፣ የአመራር ኃላፊነቱንና ሥልጣኑን ለብቻው ለመያዝ ሲሞክር ከፍተኛ ችግር እንደደረሰበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የትሮ፣ የሙሴ ዐማች ሊጎበኘው በመጣበት ወቅት ሙሴ በአስ ተዳደሩ ላይ የነበረውን ጉድለት (ድካም) አይቶ ዝም በማለት ፈንታ ጠቃሚ ምክር ሰጠው። *"ይህ የምታደርገው ነገር ሁሉ ትክክል አይደለም፤ አንተን ራስህንም ሆነ ሕዝቡን በከንቱ ታደክማለህ፤ ብቻህን ሆነህ ይህን ሁሉ ለመሥራት ይከብ ድብሃል፤ እነሆ እኔ አንድ ነገር ልምከርህ፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል፤ ሕዝቡን ወክለህ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብህና ጉዳያቸውንም በፊቱ ማቅረብህ ትክክል ነው፤ አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ልታስተምራቸው፣ እንዲሁም እንዴት መኖርና ምን ማድረግ እንደሚገባቸውም ልትገልጥላቸው ይገባል፤ በተጨማሪ ግን ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መርጠህ በሕዝቡ ላይ የሺ አለቆች፣ የመቶ አለቆች፣ የሃምሳ አለቆችና የዐሥር አለቆች አድርገህ ሹም"* አለው (ዘጸአት 18፥17-21)። ሙሴ አማቹ፣ የትሮ ጥበብ የሞላው ሰው መሆኑን ስለተረዳ፣ የሰጠውን ምክር ተቀብሎ በሥራ ላይ አዋለው።

ሙሴ የወሰዳቸው ኃላፊነቶች፣ ይፈጽማቸው የነበራቸው ሥራዎች ሌሎች ሊያደርጉት የሚችሉት መሆኑንና ኃላፊነቱንም



ለሌሎች መስጠት እንዳለበት በወቅቱ አልተረዳም ነበር። በየቀኑ ያደርግ የነበረውን ነገር ሲገልጽ፣ *"ሁለት ሰዎች ተጣልተውም ወደ እኔ ቢመጡ የትኛው ወገን ትክክል እንደ ሆነ ለማሳወቅ የእግዚአብሔርን ሕግን ትእዛዝ እነግራቸዋለሁ"* አለ (ዘጸ. 18፥16)። ይሄ ችግር የሙሴ ብቻ አይደለም። በእኛም ዘመን ያሉ አንዳንድ መሪዎች የሚያደርጉት ስህተት ነው። "ሁሉንም ሥራ እኔ ልሥራ፤ ኃላፊነቱን ሁሉ እኔ ብቻ ልውሰድ" ማለት የተለመደ የአመራር ሥርዓት ሆኗል። ኃላፊነትን ለሌሎች አለ ማከፋፈል፣ ከአስተሳሰብ ጉድለት የሚመጣ ሳይሆን፣ ደካማ ከሆነ ስሜት የሚመነጭ ነው። አንድ መሪ ጊዜውን የሚሻሙበት ነገሮች ሲበዙበት፣ ብቻውን ብዙ ነገር መሥራት እንደማይችል ሲረዳ፣ ሥራውንና ኃላፊነቱን ለሌሎች ማከፋፈል እንዳለበት ይገነዘባል። አንዳንድ መሪዎች ሥራውንና ኃላፊነቱን ለሌሎች የማያከፋፍሉበት ዋናው ምክንያት ሥራው እነርሱ በሚፈልጉት ዓይነት አይሠራም ብለው በማሰብና በመፍራት ነው። የሙሴም ችግር ይህ ነበር። አማቱ የትሮ እስከ መከረው ድረስ፣ ሌሎች ሊሠሩት ይችላሉ የሚል እምነት አልነበረውም። *"አንተን ራስህንም ሆነ ሕዝቡን በከንቱ ታደክ ማለህ ብቻህን ሆነህ ይህን ሁሉ ለመሥራት ይከብድብሃል"* (ዘጸ. 18፥18) ሲለው፣ "ሥራንና ኃላፊነትን በማከፋፈል" (delegation) የሚያምን መሪ የሚያስበው አሳብ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ሙሴ ሥራውንና ኃላፊነቱን ብቻውን ለመሸከም ሲሞ ክር ራሱን ከማድከሙም ሌላ፣ ሕዝቡም በጠቅላላው የእግዚአ ብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳይኖረው፣ የአስተዳደር ልምምድ እንዳያገኝ መከልከሉ ነበር። አንድ አማኝ "የማስተዳደር ስጦታ" ቢኖረውም፣ ስጦታውን በተግባር በማዋል ማሳደግ እንዳለበት መዘንጋት የለብንም። መንፈስ ቅዱስ ለምዕ መናኑ የሰጠው የተለያየ ስጦታ በተግባር ላይ እንዲውልና

ምዕመናኑም ስጦታቸውን እንዲያሳድጉ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ የአገልግሎት በር መክፈትና ማሰማራት ትልቁ ኃላ ፊነታቸው እንደሆነ የታወቀ ነው። ሁሉንም ሥራ መሪዎች ብቻ ከሠሩት፥ ምዕመናኑ በአገልግሎት ውስጥ የማደግ ዕድል አይኖራቸውም።

## 2.1. ሥራንና ኃላፊነትን ለሌሎች ማከፋፈል (delegation)፥ ዓለማዊ ጥበብ አይደለም

አንዳንድ አማኞች ከሌሎች የበለጠ "መንፈሳዊ" ለመም ሰል ሥርዓት ያለው ነገር፥ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያመጣ ጥሩ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲያዩ፥ "እባካችሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዓለም አሠራር አታምጡ" በማለት ይቃወ ማሉ። ስለ አስተዳደር ሥርዓት ትምህርት፥ ኃላፊነትንና ስልጣ ንን ስለ ማከፋፈል ሲሰሙ፥ "ይሄ መንፈስ ቅዱስ የሌለበት የዓለም ዕውቀት ነው" ይላሉ። እርግጥ ነው "መንፈስ ቅዱስ ምን ይላል?" ብሎ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን በመፈለግ ፈንታ፥ "ኤክስፐርቶች" ምን ይላሉ? ወደማለቱ የሚያደሉ ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆኗ ቀርቶ ሌላ መልክ ትይዛ ለች። አስፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ፥ የክርስቶስ ቤተ ክርስ ቲያን መንፈሳዊ አካል መሆኗ ቀርቶ "ዓለማዊ ድርጅት" እን ድትመስል እንደሚያደርጋት የማያጠራጥር እውነት ነው። ይሁን እንጂ "ኃላፊነትንና ሥልጣንን ለሌሎች ማከፋፈል" (delegation) መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን አሳብ አይደለም። የሚያስደንቀው፥ መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጥንቃቄ ብንመረምር፥ የዘመኑ "የአስተዳደር ሳይንስ" ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ እንዳለበት እናያለን። ለዚህ ጥሩ ምሳሌያችን ቀደም ሲል የተ መለከትነው የትሮ ለሙሴ የሰጠው የአስተዳደር ምክር ነው።

የትሮ ለሙሴ ያንን የመሰለ ምክር ሲሰጠው፥ ሙሴ



የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተላለፍ፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንዲሆን ፈልጎ አይደለም። እንዲያውም ምክሩ ከእግዚ አብሔር ጋራ የሚያቀራርበው እንደሆነ አምኖ ነው። "እነሆ እኔ አንድ ነገር ልምክርህ፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆ ናል" አለው (ዘጸ. 18፥19)። መንፈስ ቅዱስ በሙሴ በኩል እንደሚናገር፥ በየትሮም ውስጥ መናገር ይችላል። ብዙ መሪዎች የሌሎችን ምክርና አሳብ መስማትና መቀበል አይሆንላቸውም። ሙሴ ግን ይህን ዓይነት ችግር አልነበረበትም። ሙሴ የአማቱን የየትሮን ምክር በመስማቱ እግዚአብሔር ሲቆጣው፥ ወይንም ሲገስጸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናይም። እንዲያውም የየት ሮን ምክር በተግባር ላይ በማዋሉ እግዚአብሔር የበለጠ እንደ ባረከው እናያለን። እግዚአብሔር ሁልጊዜ አገልጋዮቹን የሚና ገርበት የተለያየ መንገድ አለው። አንደኛው በሌሎች በኩል የሚመጣ መልካም ምክር ነው። ይህንን በመረዳት ሙሴ የአ ማቱን የየትሮን ምክር እንደሚገባው ተጠቀመበት።

## 2.2. ሥራንና ኃላፊነትን ለሌሎች ማከፋፈል፥ ራስን ከኃላፊነት ነጻ ማድረጊያ አይደለም

ሙሴ ሥራውንና ኃላፊነቱን ለሌሎች ካከፋፈለ በኋላ፥ እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት ትቶ እጁን አጣምሮ አልተ ቀመጠም። እርሱም የራሱ የሥራ ድርሻ ነበረው። ሥራውንና ኃላፊነቱን ለብዙዎች በማከፋፈሉ፥ በአስተዳደሩ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን አደረገው። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማስተማር፥ እንዴት መኖርና ምን ማድረግ እንደሚገባቸውም ማስተማሩን ቀጠለ። መሪ ሥራውንና ሥልጣኑን ለሌሎች ማከፋፈል ይቻል እንጂ፥ ተጠያቂነትን ግን (accountability) ለማንም ማስተ ላለፍ አይችልም። ይህም ማለት፥ ሥራውን እንዲሠሩ የተወ ከሉት ሰዎች የተሰጣቸውን ሥራ እንደሚገባ ባይፈጽሙ፥ ሥራው

ባለመሠራቱ ምክንያት መሪው “ተጠያቂ” አይሆንም ማለት አይ ደለም። “ችግሩ ከእኔ አይደለም፤ ኃላፊነት የሰጠሁት ሰው ስላ በላሸ ነው” ብሎ ምክንያት መስጠት አይችልም። ይህንን ስለ ሚፈሩ ነው ብዙ “መሪዎች” ሥራውን ለሌሎች በማከፋፈል ፈንታ ብቻቸውን ለመሥራት የሚፈልጉት። ይሁን እንጂ፣ ትክክለኛ አመራር አይደለም።

## 2.3. *ሥራንና ኃላፊነትን ማከፋፈል፣ ችሎታ ላላቸው ሰዎች መሆን አለበት*

“የማስተዳደር ስጦታ” ያለው ሰው፣ ሥራውንና ኃላፊነ ቱን ለእነማን ማከፋፈል እንዳለበት ያውቃል። በዘመናችን በየ ቤተ ክርስቲያኑ ያለቦታቸው ተመድበው የሚያገለግሉ አማኞች ብዙ እንዳሉ እናውቃለን። በቤተ ክርስቲያናችውም ለሚፈጠረው ችግር ከምክንያቶቹ መካከል አንደኛው ይሄ ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ምዕመናኑን በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ የሚያስቀምጡት፣ ስጦታ እንዳላቸው አይተው ሳይሆን፣ የማይቃወሟቸውን፣ ወይም የሚደግፏቸውን አማኞች ብቻ ነው። አገልግሎት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ኃላፊነት እንጂ፣ በሹመት መልክ ከሰዎች የሚሰጠን አይደለም። አንዳንድ መሪ ዎች ደግሞ “አገልግሎትን” የሚቃወማቸውን ሰው ዝም ማሰኛ አድርገው ሲጠቀሙበት እናያለን። “በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለምን እንዲህ ዓይነቱ ነገር ይኖራል? እያለ ብዙ ጥያቄ ይጠ ይቅ የነበረው አማኝ፣ የአገልግሎት በር ሲከፈትለት፣ ጥያቄ መጠየቁን አቁሞ ተስማምቶ መኖር ይጀምራል። ተስማምቶ መኖር ብቻ ሳይሆን፣ የመሪዎች ጠባቂ (ቦዲ ጋርድ) ይሆናል።

እንደ እግዚአብሔር ቃል የሕዝቡ መሪ ለመሆን የተጠሩ፣ የትኛው አማኝ በየትኛው አገልግሎት ውስጥ መግባት እንዳለበት



መንፈስ ቅዱስ ይመራቸዋል፤ አስፈላጊውን ጥበብና ማስተዋ ልንም ይሰጣቸዋል። የትሮ ሥራውንና ኃላፊነቱን እንዲያከፋፍል ለሙሴ ሲነግረው፣ ኃላፊነቱን የሚረከቡት ሰዎች፣ ችሎታና መንፈሳዊነት የሌላቸው ቢሆኑ ምንም አይደ ለም አላለውም። *“ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መርጠህ...እነርሱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ እምነት የሚጣልባቸውና በጉቦም የማይደለሉ ሰዎች መሆን አለባቸው”* አለው (ዘጸ. 18፥21)። ጥሩ መንፈሳዊ አቋም እንዳላቸው ሳይመረምሩ ሰዎችን በኃላፊነት ላይ ማስቀመጥ፣ ያለንን የአስተዳደር ድክመት ያሳያል።

## 2.3. *ሥራንና ኃላፊነትን ማከፋፈል፣ ሰላም ያለው የአስተዳደር ሥርዓትን ይፈጥራል*

እግዚአብሔር የሥርዓት እንጂ የሁከት አምላክ አይደ ለም። ሕዝቡን እንዲመሩ ኃላፊነት የሚሰጣቸው መሪዎች በሥነ ሥርዓት የሚመሩ እንዲሆኑ ይፈልጋል። የትሮ ለሙሴ የሰጠው “የአስተዳደር ሥርዓተ ምክር” ቢሮክራሲ የበዛበት አሳብ አይደ ለም። የትኛው፣ ለየትኛው ተጠሪ እንደሆነ፣ በግልጽ ይታወ ቃል። ሙሴን ማነጋገር የሚፈልጉ ቢኖሩ፣ ብዙ ሰዓት ደጅ ሳይጠኑ ወደ እርሱ ፊት መቅረብ ይችሉ ነበር። የትሮ ለሙሴ የሰጠው ምክር እግዚአብሔር የሚደግፈው አሳብ መሆን አለመ ሆኑ እንዲመረመር ፈቃደኛ ነበር። ለዚህ ነው፣ *“በዚህ ዓይነት ብትሠራና ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ራስህን በከንቱ አታደክምም፤ ሕዝቡም በቀላሉ ጉዳያቸው እየተፈጸመላቸው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ”* ያለው (ዘጸ. 18፥23)። የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት አስተዳደር ከሆነ፣ በሕዝቡ መካከል ስምምነት እንጂ፣ ሁከት አይፈጠርም።

## 3. ስለ "አስተዳደር ስጦታ" ማወቅ ያለብን እውነቶች

### 3.1. የአስተዳደር ስጦታና (*gift*) የአስተዳደር ደረጃ (*position*) አንድ ዓይነት አይደለም

ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት አያውቁም። ሰዎች የመሪነት ስልጣን ሲሰጣቸው፥ ወዲያው መሪዎች እንዲሆኑ የሚያስችላቸው ችሎታ እንዲኖራቸው ይመኛሉ። ይሁን እንጂ፥ ሽማግሌ ሆነው በመመረጣቸው ብቻ የአስተዳደር ችሎታ (ስጦታ) ያገኛሉ ማለት አይደለም። የሚያስደንቀው ነገር "የማስተዳደር ስጦታና ችሎታው ያላቸው" ሰዎች ብዙ ጊዜ፥ የኃላፊነት ቦታ እንዲይዙ ሲጠየቁ "እምቢ!" ሲሉ፥ ችሎታው የሌላቸው ግን ቦታውን ለመያዝ ሲሯሯጡ ያታያሉ። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአስተዳደር ስጦታውም ሆነ ችሎታው እንደሌላቸው በግልጽ ያስታውቃል። የሚያሳዝነው፥ ልክ የመሪነቱን ሥፍራ ሲይዙ ሁሉን የሚያውቁ ይመስላቸውና ከሌላው ለመማር ፈቃደኞች አይሆኑም። የመሪነት ወይንም የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው አማኞች፥ ሥልጣን የመፈለግ ጥማት ስለሌላቸው፥ በአስተዳደር ቦታ ላይ ባይቀመጡ እንኳን፥ ሁልጊዜ አሳብ ሲሰጡ፥ ሲመክሩ ይታያሉ።

### 3.2. የአስተዳደር ስጦታ፥ ከሰውየው ባህሪ (ማንነት) ጋር ግንኙነት የለውም

ብዙዎቻችን የአስተዳደር ችሎታን ከሰው ባህሪ (ማንነት) ጋር የማያያዝ ዝንባሌ አለን። መሪ ይሆናል፥ ወይንም የማስተዳደር ችሎታ አለው ብለን የምናስበው ሰው፥ ተጨዋች፥ ከሰው ጋር እንደልቡ ማውራት የሚችል፥ ሁለ ገብ የሆነውን ሰው ነው። እርግጥ ነው እንዲህ ዓይነት የተፈጥሮ ባህሪ ያላቸው ሰዎች ለጊዜውም ቢሆን ሰዎችን የመሳብ ችሎታ አላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ጊዜ በሕዝቡ መካከል ግጭትን አለመ



ስማማትን የመፍጠር ዝንባሌ አላቸው። ብዙዎች እንደነዚህ ዓይነቶቹን መከተል፥ ወይንም እንደ መሪ አድርገው መቀበል አይሆንላቸውም። አብዛኛዎቹ ማንም ሳይሾማቸው ራሳቸውን የሾሙ፥ የቤተ ክርስቲያን ፍሬ መርማሪዎች ናቸው። በወንድማቸው ዓይን ላይ ያለውን ጉድፍ ለሌሎች ማሳየት ደስ ይላቸዋል። ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን የሾሙ፥ "ነቃፊዎች" ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትክክል ያልሆነ ውሳኔ መደረግ አለመደረጉን እንዲያዩ፥ እንዲሁም መጋቢው የሚወስነውን ውሳኔ እንዲመረምሩ እግዚአብሔር ቀብቶ ያስቀመጣቸው የሚመስላቸው ናቸው። ስለዚህ ብዙ ጊዜ ተናጋሪዎች፥ ሁለ ገብ የሆነ (*extrovert*) ባህሪ ያላቸውና "የአስተዳደር ችሎታ" የጎደላቸው ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ጢሞቴዎስ በባህሪው ዝምተኛ፥ ረጋ ያለ (*introvert*) ሰው እንደነበረ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ፥ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አንዱ መሆን ብቻ ሳይሆን፥ በአገልግሎቱ ብዙዎችን የነካ ሰው እንደነበረ የተመሰከረለት ነው። ጳውሎስ የጢሞቴዎስን ዝምተኛነት ስለ ተረዳ ይመስላል *"...እጆቼን በአንተ ላይ በጫንሁ ጊዜ የተሰጠ ሀንና የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣው አሳስብሃለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠን የኀይልና የፍቅር፥ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አይደለም"* ያለው (2ኛ ጢሞ. 1፥6-7)። ጢሞቴዎስ ትንሽ ፈሪ መሆኑን ቢያውቅም፥ በአስፈላጊው ጊዜ የፊልጵስዩስ አማኞችን እንዲመክርና እንዲያጽናና ጳውሎስ ላከው። *"...ጢሞቴዎስን በፍጥነት ወደ እናንተ ለመላክ እንደሚያስችለኝ በጌታ ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ"* ይላል (ፊል. 2፥19)። የተሰሎንቄ አማኞችም እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ጳውሎስ የላከው አሁንም ጢሞቴዎስን ነው። *"... የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልከንላችኋል፤ የላክንላችሁም እንዲያጸናችሁና በእምነት እንድ ትበረቱ ይመክራችሁ ዘንድ ነው"* አለ (1 ተሰ. 3፥2)።

### 3.3. የንግግር ችሎታ ያላቸው ሁሉ፥ የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው አይደሉም

የአስተዳደርን ስጦታ፥ ወይንም ችሎታን ከንግግር ችሎታ ጋር የሚያይዙ አሉ። በንግግሩ ቀልጣፋ ከሆነ፥ የመምራት ችሎታ አለው ብለው ያስባሉ። ይህ እውነት እንዳልሆነ ከሙሴ ሕይወት መረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር ሙሴን ለከፍተኛ አገልግሎት ሲጠራው፥ ሙሴ የሰጠው ምክንያት *"እኔ አንደበቴ የሚኮላተፍና አፍርቼ ለመናገር የማልችል ነኝ"* የሚል ነበር (ዘጸ. 4፥10)። ይህንን እውነት ባለመረዳት፥ በንግግር ቀልጣፋ የሆኑ አንዳንድ አማኞች ያለስጦታቸውና ያለችሎታቸው በመሪነት ቦታ እንደተቀመጡ እናውቃለን። በንግግር ቀልጣፋነት ቤት ክርስቲያን መመራት ብትችል ኖሮ፥ በዘመናችን በየአብያተ ክርስቲያኑ የምናየው ችግር አይፈጠርም ነበር፤ ለተፈጠረውም አንዳንድ ችግር መፍትሄ ይገኝለት ነበር።

### 3.4. መሪ የሚሆኑት፥ "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ብቻ ናቸው ማለት አይደለም

*"የማስተዳደር ስጦታ"* ያላቸው አማኞች መሪ ቢሆኑ፥ የመሪነት አገልግሎታቸው ፍሬያማ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፥ በማንኛውም የመሪነት ስፍራ ከመቀመጣቸው በፊት "የማስተዳደር ስጦታ" እንዳላቸው መታየት አለባቸው አንልም። ብዙዎቻችን "የመስጠት ስጦታ" ስለሌለን መስጠት አንችልም ማለት አይደለም። "የወንጌላዊነት ስጦታ" ስለሌለን ላልዳኑት ሰዎች መመስከር የለብንም ማለት አይደለም። ልክ እንደዚሁ "የአስተዳደር ስጦታ" ስለሌለን በመሪነት አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ አንችልም ማለት አይደለም። እናት ለልጆቿ መሪ ነች፤ አባትም የቤቱ መሪ ነው። በተለያየ የሕይወት ልምምድ ውስጥ በማለፍ "የአስተዳደር ችሎታ" ሊኖረን ይችላል።



"የማስተዳደር ስጦታ" ያለው ግን፥ ስጦታው ስላለው በቀላሉ መሪ መሆን ይችላል። በአመራሩም ጥሩ ፍሬ ያያል። ሰዎችም በመሪነቱ ያምናሉ።

### 3.5. መሪነት፥ ከሥልጣን ጋር አይያያዝም

ኢየሱስ በምድር በነበረው በሦስት ዓመት ተኩል የአገልግሎት ዘመኑ፥ ሰፊውን ጊዜ ያጠፋው አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር፥ ወደፊት ለምትመሠረተው ቤተ ክርስቲያን ጥሩ መሪዎች (አስተዳዳሪዎች) እንዲሆኑ በማዘጋጀት ነበር። ይሁን እንጂ፥ ደቀ መዛሙርቱ አልፎ አልፎ የራሳቸው የሆነ የአመራር ችግር እንደነበረባቸው እናውቃለን። "አገልግሎቱን" በመመኘት ፈንታ "ሥልጣኑ" ላይ ትኩረት ይሰጡ ስለነበረ ሌላው ቀርቶ እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ ምክንያት ሆኖባቸው ነበር። ያዕቆብና ዮሐንስ መሪነትን ከሥልጣን ጋር በማያያዛቸው፥ ከፍተኛውን ስልጣን እንዲሰጣቸው ኢየሱስን ጠየቁት። የተቀሩት ደቀመዛሙርት የዮሐንስንና የያዕቆብን ጥያቄ ሲሰሙ ተቆጡ። ኢየሱስም የተፈጠረውን ግጭት ለማብረድ ሁሉንም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው። "የአረማውያን አለቆች የሕዝብ ገዥዎች ተብለው እንደሚጠሩና መሪዎቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣን እንዳላቸው ታውቃላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ መሆን አይገባም፤ ከመካከላችሁ ትልቅ ሊሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ መሆን አለበት፤ እንዲሁም ከመካከላችሁ የበላይ ሊሆን የሚፈልግ የሁሉም አገልጋይ ይሁን" አላቸው (የማር. 10፥42-44)።

## 4. "የማስተዳደር ስጦታ" ያለው በምን ይለያል?

### 4.1. በኃላፊነት የተሰጣቸውን ሥራ የማቀናበር ንቃት ይታይባቸዋል

*"የማስተዳደር ስጦታ"* ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ደስታ የሚሰጣቸው በቀላሉ ሠርተው የሚጨርሱት ሳይሆን፥ በኃይል

ታግለው ከፍጻሜ ሲደርስ የሚያዩት ሥራ ነው። በእነርሱ ኃላፊ ነት ሥር ያለውን ማደራጀት፥ ማሳደግ በጣም ደስ ይላቸዋል። የሚሠሩት፥ "አድርጉ" ተብለው፥ ወይንም በትዕዛዝ ሳይሆን፥ በግል ፍላጎታቸው ተነሳስተው ነው። ሰዎችን፥ ዕቃን፥ ጊዜን በማቀናጀት፥ በማያያዝ፥ እንዲብቃቃ በማድረግ፥ ዕቅድ በማ ውጣት ልዩ የሆነ ችሎታ አላቸው። ሥራው በተቀላጠፈ መልክ እንዲሄድ ኮሚቴ መፍጠር፥ ማስተባበር፥ ኃላፊነታቸውን መደ ልደል፥ እንዲሁም አዳዲስ ፕሮጀክት ጀምረው የመጨረስ ችሎታ ያላቸው ናቸው። ብዙ ጊዜ በሚሠሩት ሥራ ቀልጣፋ በመሆናቸው፥ አብረዋቸው የሚ ሠሩም ሆነ የሚያገለግሉ ሰዎች በእነርሱ አካባቢ መሆን፥ አብሮ መሥራት አያዝናናቸውም። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ ሰዎች በእነርሱ ላይ ሲያጉረመርሙ ይሰማሉ።

### 4.2. ለነቀፋ አይበረግጉም

በአስተዳደር ወይንም በመሪነት ቦታ ላይ የሚቀመጥ ሰው፥ ብዙ ጊዜ ትክክለኛ የሆነም ያልሆነም ነቀፋ እንደሚደር ስበት የታወቀ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ "ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ከባድና አስቸጋሪ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት፥ ሰዎች ስላሉበት ነው። ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ደግሞ ሁልጊዜ ችግር አይጠፋም" አለ። ስለዚህ በአስተዳደር፥ ወይንም በመሪነት ቦታ የሚያገለግል ማንኛውም ሰው የሚቀምሰው የራሱ የሆነ መራራ ጽዋ አለው። በሥልጣን ላይ በተቀመጡ ሰዎች ላይ ጥሩም ሆነ መጥፎ አስተያየት መስጠት የተለመደ ነው። ቀስ ብለው ከሠሩ፥ ለምን አይፈጥኑም፥ ከፈጠኑ ደግሞ ለምን ቀስ ብለው በጥንቃቄ አይሠሩም፥ በማለት አስተያየት ይሰጥባ ቸዋል። ለዚህ ነው የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት አብርሃም ሊንከን፥ *"ሰውን ሁሉ አንዳንድ ጊዜ፥ ጥቂቶቹን ሁልጊዜ*



*ማስደሰት ይቻላል። ሁሉን ሰው፥ ሁልጊዜ ማስደሰት ግን አይቻልም"* ያሉት። ይሁን እንጂ፥ "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች፥ ተነቀፍኩ ብለው ሊሠሩ የተነሱበትን ሥራ ወይም ኃላፊነት ጥለው አይሄዱም። ስጦታው የሌላቸው ሰዎች ግን፥ "ነቀፋን" ታግሰው ለረጅም ጊዜ ማገልገል አይችሉም።

### 4.3. ሥራንና ሥልጣንን ለሌሎች ማከፋፈል ይወዳሉ

"የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ ሥራውን ሁሉ ለብቻ ቸው መሥራት አይፈልጉም። ከሌሎች ሰዎች ጋር መሥራት ደስ ይላቸዋል። መሠራት ያለበትን ነገር ማየትና ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ እነማን ቢሠሩት የተሻለ ውጤት ያመጣሉ በማለት የሌሎችን አቅምና ችሎታ መመዘን ይችላሉ። ሥራውን ለሌሎች የሚያከፋፍሉት፥ ለሰዎች ሥራ ለመፍጠር፥ ራሳቸውን ከሥራና ከኃላፊነት ነጻ ለማድረግ ብለው ሳይሆን፥ ሥራንና ሥልጣንን ማከፋፈል ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣ ስለሚያም ኑበት ነው።

"የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያ ንም ሆነ መንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ በተለያየ መስክ ተሰማርተው ከሚያገለግሉት መካከል፥ ያለአግባብና ያለቦታቸው በመቀመጥ ውጤት የሌለው ሥራ የሚሠሩትን፥ ገለል ያደርጋሉI ጥሩ የሚ ሠሩትን ደግሞ ቁልፍ፥ ቁልፍ ቦታዎችን በመስጠት ሥራውን እንዲሠሩ ያደርጋሉ። የአመራር ሥርዓት በማስተማርም የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል።

### 4.4. "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ ሀሳባቸውን ጥሩ አድርገው መግለጽ ይችላሉ

መናገር የሚችሉ ሁሉ "የማስተዳደር ስጦታ" እንደሌ ላቸው ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይህን ስንል የንግግር ችሎታ

ለአስተዳደር አስፈላጊ አይደለም ማለታችን አይደለም። "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ ሀሳባቸውን ጥሩ አድርገው የመግለጽ ችሎታ አላቸው። ምን ለማድረግ እንደፈለጉ፥ ምን ዓይነት ዕቅድ እንዳላቸው ጥሩ አድርገው ማስረዳት ይችላሉ። ሀሳባቸውን የበለጠ ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ቻርት፥ ዳያግራም፥ ግራፍና የመሳሰሉትን የመጠቀም ችሎታ አላቸው።

### 4.5. ራሳቸውን ከሌላው ባለሥልጣን ሥር ማድረግ፥ ቅር አይላቸውም

"የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ ከእነርሱ በላይ የሆኑትን ባለሥልጣናት ማክበር፥ ከእነርሱ ትዕዛዝ መቀበል አይከብዳቸውም። በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በመንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ ባለው መዋቅር ውስጥ ከየትኛውም ደረጃ ላይ ቢሆኑ ግድ የላቸውም። አንድ ጊዜ አገልጋዩ ታሞበት ኢየሱስ እንዲፈውሰው የጠየቀው የመቶ አለቃ "የማስተዳደር ስጦታ" ሳይኖረው እንዳልቀረ እንገምታለን። ኢየሱስ "እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ" ሲለው፥ *"ጌታ ሆይ! አንተ ወደ ቤቴ እንድትገባ የበቃሁ ሰው አይደለሁም፤ ነገር ግን አንዲት ቃል ብቻ ተናገር አገልጋዬም ይድናል። እኔ ራሴ ለባለ ሥልጣኖች ታዛዥ ስሆን ከእኔ በታች የማዛቸው ወታደሮች አሉኝ፤ ከእነርሱ አንዱን ሂድ! ስለው ይሄዳል፤ ሌላውንም ና! ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬም ይህን አድርግ ስለው ያደርጋል"* አለ (የማቴ 8፥8-9)። "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች፥ ወሰናቸውን ስለሚጠብቁ ያላቸውንና የሌላቸውን ሥልጣን ማወቅ ይፈልጋሉ። ይህንን የሚያደርጉት ከመሥመር እንዳይወጡ ራሳቸውን ለመጠበቅ፥ ባላቸውም ነጻነት ደግሞ እንደልባቸው ለመሥራትና ለሚሠሩት ሥራ የራሳቸው አለቃ መሆን እንዲችሉ ነው።



### 4.6. ከተሰጣቸው ኃላፊነት ውጪ፥ ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይወስዱም

"የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች፥ የሥልጣን ጥማት ስለሌላቸው፥ ከተሰጣቸው የኃላፊነት ድንበር ውጪ መውጣት አይፈልጉም። ከእነርሱ በላይ የሆነ ባለሥልጣን እንዲሠሩ ካልጠየቃቸው በስተቀር፥ ያንን ሥራ ለመሥራት ችሎታ እንዳላቸው ቢያውቁም፥ አይሠሩም። ራሳቸውን ለበላይ ማስገዛት እንደ ሸክም ሆኖ አይሰማቸውም። ኃላፊነት የሚወስዱት፥ ሌላ በመሪነት ደረጃ ያለ ሰው ከሌለ ብቻ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በመንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ፥ ሁኔታውን የሚያስተካክል መሪ ከሌለ፥ "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች፥ ማንም ሳይጠይቃቸው ሁኔታውን መልክ ለማስያዝ ሳይፈሩ ይገባሉ።

### 4.7. ሌሎች ሲመሰገኑ ቅር አይላቸውም

"የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ በሚሠሩት ሥራ ሌሎች ምስጋናውን ቢቀበሉ፥ ሥራው ይሠራ እንጂ ፍጹም ግድ የላቸውም። በተሠራው ሥራ መመስገንን አይወዱም ማለት አይደለም። ምስጋናውን አብረዋቸው ከሠሩት ጋር መካፈል ቅር አይላቸውም። ብዙ ጊዜ ከሌሎች ጋር መሥራት የማይፈልጉ ሰዎች፥ ምስጋናውን ከሌሎች ጋር መካፈል የማይወዱ ናቸው። እውነተኛ መሪ፥ "ውጤቱ ያማረ መሆን የቻለው፥ ብቻዬን ሠርቼ ሳይሆን፥ ብዙዎች አብረውኝ በመልፋታቸው ስለሆነ፥ ሊመሰገኑ ይገባል" ለማለት አይከብደውም።

### 4.8. ባለ ራዕይ ነው

"የማስተዳደር ስጦታ" ያለው፥ ሁኔታን ሰፋ አድርጎ መመልከት ይችላል። የዛሬውን ብቻ ሳይሆን፥ የነገውንም

ያያል። ሕዝቡን እንዴት አድርጎ እንደሚመራ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ራዕይ አለው። *"ከእግዚአብሔር መመሪያ የማያገኝ ሕዝብ ሥርዓት የጎደለው ይሆናል"* ይላል (ምሳ. 29፥18)። የድሮው ትርጉም "ራዕይ" ሲለው፥ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ግን "መመሪያ" ይለዋል። ጥሩ መሪ፥ ሕዝቡ ከየት ተነስቶ የት መድረስ እንዳለበት በግልጽ የሚያሳይ "ራዕይ" ወይንም "መመሪያ" ያለው ነው። ራዕይ ወይም መመሪያ ስንል፥ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ መንፈሳዊ ድርጅት፥ ሕዝቡ እንዴት አብረው መሥራት እንደሚችሉ፥ ምን ዓይነት ዓላማ ወይም ግብ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። የነህምያ ራዕይ፥ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር መገንባት ነበር። የኢያሱ ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ አገር ማስገባት ሲሆን፥ የዮሴፍ ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ ሊመጣ ያለውን ሰባቱን የረሀብ ዘመን መወጣት የሚችሉበትን ዘዴ መፈለግ ነበር።

ራዕይ ያለው መሪ፥ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል። "የማስተዳደር ስጦታ" ያላቸው፥ ሊፈጽሙት ያሰቡትን፥ ከሌሎች ጋር አብሮ በመሥራት ከሚፈለገው አጥጋቢ ውጤት ላይ እንደሚደርሱ "እምነት" አላቸው። የሚያልሙትን ሕልም፥ ያላቸውን ራዕይ ብዙ ጊዜ የሚከተሏቸው ሰዎች እነርሱ እንደሚያዩት ያያሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን ሕዝቡ ባላቸው መሪ እምነት ካላቸው፥ ራዕዩን ለመቀበል ከባድ አይሆንባቸውም።

☆ ☆ ☆ ☆



ምዕራፍ

17

# ምሕረት የማድረግ ስጦታ

*"...ስጦታችን ምሕረት ማድረግ ከሆነ፥ በደስታ ምሕረት እናድርግ።"*

(ሮሜ 12፥8)

"ምሕረት የማድረግ ስጦታ" ጎልቶ የሚታይ፥ ወይንም ስጦታው ያለውን አማኝ በሕዝብ ዘንድ ታዋቂ እንዲሆን የሚያደርግ ስጦታ ስላልሆነ፥ ይህን ዓይነቱን ስጦታ እግዚአብሔር እንዲሰጠው የሚጠይቅ አማኝ ይኖራል ለማለት ያስቸግራል። "የፈውስ፥ ተአምር የማድረግ፥ በልዩ ልዩ ቋንቋ የመናገር ስጦታዎችን" ለማግኘት የምንመኘውንና የምንፈልገውን ያህል፥ ጎልተው የማይታዩትን ስጦታዎች ለመቀበል አንመኝም። "በልዩ ልዩ ቋንቋ የመናገር ስጦታ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?" የሚለውን ጥያቄ በደብዳቤ ብዙዎች ይጠይቁኛል። *"የምሕረት ስጦታ"* ወይም ሌሎች በአደባባይ በግልጽ የማይታዩትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንዴት ማግኘት እችላለሁ የሚል